# አማርኛ
# እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## 6ኛ ክፍል


**አዘጋጆች**

በላይነሽ ደነቀ (ዶ/ር.)

ታሪኩ ነገሰ (ዶ/ር.)

**አርታኢዎች**

ትንሳኤ ጀምበሬ

ንጉሴ ዴአታ

**ጥራት ተቆጣጣሪዎች**

ይልፋሸዋ ጥላሁን

በርናባስ ደበሎ

ታምሩ ገለታ

**ግራፊክስ እና ምስል ገለፃ**

ሰለሞን አለማየሁ ጉተማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2014 ዓ.ም.

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

የቅጂ መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# ማውጫ


ማውጫ ..... iii

መግቢያ ..... iv

ምዕራፍ አንድ ..... 1

ባህላዊ ልብሶች ..... 1

ምዕራፍ ሁለት ..... 12

ዝነኛ አትሌቶች ..... 12

ምዕራፍ ሦስት ..... 22

ቃላዊ ግጥሞች ..... 22

ምዕራፍ አራት ..... 30

ዘመናዊ ግብርና ..... 30

ምዕራፍ አምስት ..... 37

ቱሪዝም ..... 37

ምዕራፍ ስድስት ..... 44

ፀረአደንዛዥ ንጥረነገሮች ..... 44

ምዕራፍ ሰባት ..... 51

የጥላቻ ንግግር ..... 51

ምዕራፍ ስምንት ..... 59

ኤችአይቪ/ኤድስ ..... 59

ምዕራፍ ዘጠኝ ..... 66

ልማዳዊ ተግባራት ..... 66

ምዕራፍ አሥር ..... 74

ሴቶችን ማብቃት ..... 74

አማርኛ እንደ አፍመፍቻ ቋንቋ የ6ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ..... 82

መግቢያ ..... 82

ዋቢዎች ..... 103

# የመምህር መምሪያ

# ስድስተኛ ክፍል

## መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያ የተዘጋጀው በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ተማሪዎች ማስተማሪያ የተዘጋጀውን 'የተማሪ መፅሐፍ' መሠረት በማድረግ ነው። በመሆኑም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች እንዴት ማስተማርና ተግባራቱን (መልመጃዎቹን) እንዴት ማሠራት እንደሚገባ ሁሉአቀፍ የሆነ ጥቆማ ለመምህር ያቀርባል። ከዚህም ሌላ የክፍል አደረጃጀትና አስተዳደሩ ምን መሆን እንደሚገባው አቅጣጫ ያስቀምጣል። በዚህም መምህራን የየክፍላቸውንና የየተማሪዎቻቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት መምሪያውን ተግባራዊ ያደርጉታል ተብሎ ይጠበቃል።

## የመምሪያው አደረጃጀትና ይዘት

ይህ የመምህር መምሪያ ከላይ እንደተገለፀው የተማሪ መጽሐፍን በመንተራስ የተዘጋጀ በመሆኑ የይዘት አደረጃጀቱም ይህንኑ የተከተለ ነው። ስለሆነም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተቀመጡት ምዕራፎች በቅደም ተከተል ቀርበውበታል። በየምዕራፉ ለሚከናወኑ የማዳመጥ ተግባራት የተዘጋጁት ምንባቦችም በመምህር መምሪያው ተካተዋል። አስፈላጊ ይሆናሉ ተብለው በታሰቡ ይዘቶች ላይም ተጨማሪ ማስታወሻዎች የተሰጡ ሲሆን፣ በየደረጃው ለቀረቡ መልመጃዎችም ናሙና መልሶች እንዲካተቱ ሆኗል። እነዚህ ናሙና መልሶች የቀረቡትም በቋንቋ ትምህርቱ አሰጣጥ ወቅት ወጥነት ያለው አካሄድ እንዲኖር ታስቦ ሲሆን፣ መምህርና ተማሪዎቹ እንደየሁኔታው (አውዱ) የሚያቀርቧቸው ተጨማሪ ምላሾችም ከግምት የሚገቡ ናቸው።

## ልዩ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦች

- ✓ የየትኛውም ክፍለጊዜ ትምህርት ሲቀርብ አራቱን የቋንቋ መሠረታዊ ክሂሎች በተመጣጠነና በተቀናጀ መልኩ ያካተተ ሊሆን ይገባል፤
- ✓ የትምህርቱ አቀራረብ አሳታፊ፣ ትብብራዊ እና ተግባቦታዊ የማስተማር ዘዴ መርህን የተከተለ ሊሆን ይገባል (ለምሳሌ ተማሪን ማዕከል ያደረገ መሆን)፤
- ✓ የልሥራ፣ እንሥራ፣ ሥሩ አካሄድ ሁልጊዜም ይተግበር፤ በተለይ አዲስ ርዕሰ ጉዳይና መልመጃ ሲቀርብ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፤
- ✓ ሁሉም ተማሪዎች ከተመሳሳይ ዳራ ያልመጡ ወይም ተመሳሳይ ልምድ የሌላቸው ስለሚሆን በመማር ወቅት የሚቸገሩ ተማሪዎችን ቀስ በቀስ የማብቃት ስልትን (scaffolding) በመተግበር ማገዝ ያስፈልጋል፤

- ✓ ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው ተማሪዎችና ላቅ ያለ አፈፃፀም የሚያሳዩ ተማሪዎች ሲያጋጥሙንም ችሎታዎቻቸውን ለማዝለቅ ማበረታትና ተጨማሪ ተግባራትን እያዘጋጀን በመምጣት ማትጋት ይገባል፤
- ✓ በክፍል ተሳትፎ ወቅት ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድን መከተል ይገባል (የባህል፣ የሀይማኖት፣ የፆታ ወዘተ አካታችነትን ከግምት ማስገባት)
- ✓ ተማሪዎቹ በሚማሩበት አካባቢ በሌላ መልኩ የሚተረጎም ቃል ወይም አገላለፅ ወይም ምስል ሲያጋጥም (ታቡ የሆነ) በሌላ መተካት/ማለዘብ
- ✓ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የአካቶ ትምህርትን መርህ በመከተል ተገቢ እገዛ ሊያደርጉላቸው ይገባል።

# ምዕራፍ አንድ

## ባህላዊ ልብሶች (18 ክፍለጊዜ)

### 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- ዓረፍተነገር ለመመስረት የሚያስችሉ የቃላት አፃፃፍ ህጎችን አዳምጠው ይገልጻሉ፤
- አቀላጥፎ ማንበብን ይለማመዳሉ፤
- በዓረፍተነገር ውስጥ ላሉ ውስብስብ ቃላት ትርጉም ይሰጣሉ፤
- ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀ ፅሑፍ ውስጥ የሚገኝ ፍቺን ለመረዳት ተገቢ ንበትንና ስርዓተ ነጥቦችን ያነባሉ፤
- ቃላትን እየነጣጠሉ ያነባሉ።

### 2. የትምህርት ይዘት

#### 2.1. ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- ስለሽመና ሌሎች ሲናገሩ ማዳመጥ
- መምህሩ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላቸውን ማዳመጥ
- ባዳመጡት መሠረት ጥያቄዎችን መመለስ

#### 2.2. ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- አያያዥ ቃላትን እየተጠቀሙ መናገር

#### 2.3. ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

- ለቁልፍ ቃላት የሰጡትን ፍቺ ማንበብ
- ለአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በጽሑፍ የሰጡትን መልስ ማንበብ
- ለቃላት የሰጡትን አውዳዊ ፍቺ ማንበብ
- "የወሎ ኦሮሞ ባህላዊ ልብሶች" የሚለውን ምንባብ ሥርዓተነጥቦችንና የሐረግ አከፋፈልን ተከትለው ተራበተራ ድምፅ በማሰማት ማንበብ
- "የወሎ ኦሮሞ ባህላዊ ልብሶች" የሚለውን ምንባብ ሥርዓተነጥቦችንና የሐረግ አከፋፈልን ተከትለው ተራበተራ በአንድ ደቂቃ ውስጥ በፍጥነት ማንበብ

#### 2.4. ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ ተጠቅሞ መጻፍ
- ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ዓረፍተነገር መጻፍ

#### 2.5. ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ቃላትን በተገቢ አውድ መጠቀም

- ቃላትን ማቧደን
- ቃላትን ነጣጥሎና አጣምሮ ማንበብ
- ተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ የርባታ ምዕላዶችን መለየት

### 2.6. ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው

- የወል ስምና የተጸውዖ ስሞችን መለየት
- የወል ስምና የተጸውዖ ስሞችን በመጠቀም ዓረፍተነገር መመስረት

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

ተማሪዎች የቃላት መዋቅርን ወይም የሆሄያት አሰዳደርን እንዲያነጻጽሩ የሚከተሉትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ማለማመድ፤

- ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎችንና ብልሃቶችን መጠቀም፤
- ከዝርዝር ወደአጠቃላይ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የማስተማሪያ ስልቶችን መጠቀም፤
- ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል ስለባህላዊ ልብሶች መስፋፋትና ጠቀሜታ ምክንያት እያቀረቡ እንዲወያዩ ማመቻቸት፤
- በንግግር ወቅት አያያዥ ቃላትን እንዲጠቀሙ ሞዴል ንግግሮችን በማሰማት ተማሪዎቹ ተመሳሳይ ንግግር እንዲያደርጉ ማበረታታት፤
- የሽመና መሣሪያዎችን ከተቻለ ይዞ በመምጣት ካልተቻለ ፎቶ በማሳየት ተማሪዎች እንዲያውቋቸው ማድረግ፤
- በአከባቢያቸው ያለውን ባህላዊ ልብስ ፎቶ በማንሳት ወይም ቪዲዮ በመቅረጽ ወደክፍል በማምጣት ተማሪዎቹ እንዲለዩ ማድረግ፤
- ቃላትን በጋራ መዋቅራቸው ወይም ስደራ አማካኝነት እንዲያቧድኑ በቻርት ላይ በማቅረብ ማለማመድ፤
- ተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን እንዲያወዳድሩ በቻርት አዘጋጅቶ ወደክፍል በማምጣት ማለማመድ፤
- የወል ስምና የተጸውዖ ስሞችን በቻርት ላይ ጽፈው ወደክፍል በማምጣት ማሳየትና ማለማመድ፤
- እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎችንም መጠቀም ይችላሉ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር! በትምህርት አንድ ሥር መነሻ የሚሆኑ የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው፤ የሚሰጧቸውንም ምላሾች እንዳለ ይቀበሏቸው። ተማሪዎቹ የተለያዩ መልሶችን ሊሰጡ ስለሚችሉ ለማረም መሞከር አያስፈልግም። ምላሾቹን ከተቀበሉ በኋላ ወደዋናው ትምህርት ይግቡ። በመጀመሪያ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው። በመጀመሪያው ንባብ

ተማሪዎች በጸጥታ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። በመቀጠል ንባቡን ቆም አድርገው በቦርድ ላይ የተሰጡትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እያዳመጡ መሥራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው። ከዚያም የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው። የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ የሚሠሩት በቀጣይ ክፍለጊዜ ስለሆነ ከማሠራትዎ በፊት ሀሳቡን ለማስታወስ ምንባቡን በድጋሚ ያንብቡላቸው።

## የሀገራችን የሽመና ጥበብ አጀማመር

ኢትዮጵያ በበርካታ ባህላዊ እና ታሪካዊ እሴቶች ትታወቃለች። ከእነዚህም መካከል የሕዝቦቿ ባህላዊ አለባበስ አንዱ ነው። ይህ ባህላዊ አለባበስ ደግሞ በአመዛኙ የሽመና ሥራ ውጤት ነው። ሥራው በሀገራችን መቼና እንዴት እንደተጀመረ በትክክል አይታወቅም። ይሁን እንጂ ከሺ ዓመታት በላይ ዕድሜ እንዳለው አንዳንድ ጽሑፎች ይጠቁማሉ። በፊንፊኔ በስፋት የተዋወቀው ግን ከጋሞ ተራራማ ቦታዎች በተለያዩ ምክንያቶች በመጡ የጋሞ ማሕበረሰብ አባላት ነው። ከእነዚህም ምክንያቶች በፊንፊኔ ውስጥ በርካታ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች እየተስፋፉ መምጣታቸው አንዱ ነው። ሁለተኛው ከከተማዋ የገበያ ፍላጎት ጋር ተዳምሮ ከተለያዩ አካባቢዎች የጉልበት ሠራተኞች ወደ ፊንፊኔ መምጣታቸው ነው። ከእነዚህም መካከል የጋሞ ተወላጆች ይገኙበታል። ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ የጋሞ ተወላጆች ግብር ለማስገባትና አቤቱታቸውን ለማቅረብ ወደ መዲናዋ በብዛት መምጣታቸው ነበር።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የሽመና ሥራ እንዴት ተጀመረ?

እነዚህ የማሕበረሰብ አባላትም የሽመና ሥራን የጀመሩት በተለያየ ምክንያቶች እንደሆነ ይነገራል። አንደኛው በመሠረተ ልማት ግንባታው የሚከፈላቸው ገንዘብ በቂ አለመሆኑ ነው። ሌላው ደግሞ ይዘው የመጡትን ግብርና አቤቱታ የሚያስተናግድ የቤተ-መንግሥት ባለሙያ ማጣታቸው ነው። በችግሩም ከትውልድ ቀያቸው ይዘውት በመጡት የሽመና መሣሪያ አማካይነት የሽመና ሥራ መሥራት ጀመሩ። በወቅቱ ጋሞዎች የሽመና ሥራን በሁለት መንገድ ያከናውኑ ነበር። አንደኛ ሸማ ማሠራት በሚፈልጉ ግለሰቦች መኖሪያ ቤት በረንዳ ላይ መሣሪያቸውን በማቆም ይሠሩ ነበር። ለሥራቸውም የሚከፈላቸው የዕለት ምግብ ነበር። ከሥራቸውም በኋላ አመሻሽ ላይ አሁን የአሜሪካ ኤምባሲ በሚገኝበት አካባቢ በመሄድ ያድሩ ነበር። ሁለተኛው ለቤተ-መንግሥት ባለሟሎች ተቀጥረው የሚሠሩ ነበሩ፤ የሥራቸውንም ውጤት ለቤተ-መንግሥት ባለሟሎች ያቀርባሉ። ለሽመናም የሚጠቀሙበት ጥሬዕቃ ድር፣ ማግ እና ጥለት ነበር። በብዛት የሚመረቱ ምርቶችም ጋቢ፣ ነጠላ፣ ቀምስ፣ ጥበብ ልብስ፣ ሙሉ ልብስ፣ ቡልኮ፣ መጠምጠሚያ፣ እና የመሳሰሉት ነበሩ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

### 2. ለሽመና ሥራ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎች ምንምን ናቸው?

ይሁን እንጂ ለሙያውም ሆነ ለባለሙያዎቹ በሌሎች የፊንፊኔ ነዋሪዎች የሚሰጠው ማሕበራዊ ደረጃ ዝቅተኛ ነበር። በመሆኑም ብዛት ያላቸው ሸማኔዎች ሽመናን በመተው ወደ ሌላ ሥራ ተሰማርተዋል። የጋሞ ማሕበረሰብ አባላት ግን ችግሩን በጽናት በመቋቋም ምርጥ የሽመና ባለሙያዎች የሚያስብል ደረጃ ላይ መድረስ ችለዋል። የሸማ ተፈላጊነትም እየገነነ መጣ። ሸማዎቹ በሚለበሱበት የተለያዩ አጋጣሚዎች እና ዓውዶች ላይ የተጠቃሚዎቹን ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ደረጃ ማሳየት ጀመሩ።

ምንጭ፡ (በአምሳሉ መላከ ብርሃን፤ የሽመና ጥበብ አጀማመር ታሪክ፤ ተሻሽሎ ከዊኪፒዲያ ድረገጽ በቀን 01/10/2013 ዓ.ም የተወሰደ)

## መልመጃ አንድ

በመልመጃ አንድ ሁለት የተለያዩ ትዕዛዞች ሥር ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ተማሪዎች ለቃላት አውዳዊ ፍቺ በመስጠት የሚመልሷቸው ናቸው። ሁለተኛው ደግሞ ለአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል መልስ የሚሰጡባቸው ናቸው። ጥያቄዎቹን እያነበቡላቸው ተማሪዎቹ በቃል ወይም በጽሑፍ በትዕዛዞቹ መሠረት እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች መልሶቻቸውን በምሳሌ አስደግፈው እንዲመልሱ ያድርጓቸው።

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ሥር አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው ንግግር ያደርጋሉ። ተማሪዎቹን በቡድን ያደራጇቸው፤ ከዚያም ለቡድኑ ተወካይ ያስመርጧቸው።

## ተግባር አንድ

በዚህ ተግባር ሥር አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ንግግር ለማዳበር የሚረዳ ጥያቄ ቀርቧል። ጥያቄውም ተማሪዎች ስለባህላዊ ልብሶች መስፋፋትና ጠቀሜታ በቡድን እየተወያዩ የተስማሙበትን ሀሳብ አያያዥ ቃላትን በመጠቀም በተወካዮቻቸው አማካኝነት በንግግር እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ነው። ስለዚህ ተግባሩን በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ያሠሯቸው።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር "የወሎ ኦሮሞ ባህላዊ ልብሶች" የሚል ምንባብ ቀርቧል። ተማሪዎቹ ሀሳቡን መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ራሳቸውን ጥያቄ በመጠየቅና ሀሳቦቹን ርስበርስ በማስተሳሰር ድምፅ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ይንገሯቸው። የቅድመንባብ፣ የንባብ ጊዜ እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹንም በትዕዛዞቻቸው መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## መልመጃ ሁለት

በዚህ መልመጃ ሥር ምንባብ ቀርቧል። ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ የቅድመንባብ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን በመጠየቅ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፤ የሚሠጡትንም ምላሾች ይቀበሏቸው። ካነበቡ በኋላ በሁለት ትዕዛዞች ሥር የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ባነበቡት መሠረት በጽሑፍ መልስ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም በትዕዛዞቹ መሠረታ ያሠሯቸው።

## ተግባር ሁለት

በዚህ ተግባር ሥር አቀላጥፎ ማንበብን የሚለማመዱበት ተግባር ቀርቧል። ለአቀላጥፎ ማንበብ ተግባሩ ቀጥሎ በቀረበው የመከታተያ ቅጽ መሠረት የተማሪዎችን የማንበብ ፍጥነት ይለኩ፤ የተሳሳቱትን ቃላትና የወሰደባቸውን የንባብ ጊዜ በመጨረሻ ላይ በመንገር ግብረመልስ ይስጡ።

| ያነበቡ ተማሪዎች | የተሳሳቷቸው ቃላት ብዛት | አንቀጹን ለማንበብ የወሰደባቸው ጊዜ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ½ደቂቃ | 1 ደቂቃ | 1½ ደቂቃ | 2 ደቂቃ |
| ተማሪ አንድ | | | | | |
| ተማሪ ሁለት | | | | | |
| ተማሪ ሦስት | | | | | |
| ተማሪ አራት | | | | | |
| ተማሪ አምስት | | | | | |

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ሥር ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ መጠቀም እና መነሻ ሀሳቦችን በመጠቀም ዓረፍተነገር መጻፍ ቀርበዋል። ሥርዓተነጥቦችን ለመረዳት የሚያስችላቸው ማስታወሻም ቀርቦላቸዋል። በመሆኑም የቀረቡትን መልመጃዎችና ተግባራት በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሦስት

በዚህ መልመጃ በሦስት የተለያዩ ትዕዛዞች ሥር ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ለቀረቡት ዓረፍተነገሮች ተገቢውን ሥርዓተነጥቦች በማስገባት በመጻፍ የሚመልሷቸው ናቸው። ሁለተኛው ደግሞ በቀረቡላቸው ሥርዓተነጥቦች ተጠቅመው የራሳቸውን ዓረፍተነገር የሚመሠርቱባቸው ሲሆን ሦስተኛው ደግሞ መነሻ ሀሳቦችን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን በመጻፍ የሚመልሷቸው ናቸው። በመሆኑም የቀረቡላቸውን መልመጃዎች በተሰጣቸው ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።


# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ሥር የተለያዩ ቃላትን እንዲጠቀሙ የሚያስችሏቸው ተግባራትና መልመጃዎች ቀርበዋል። ስለዚህ በትዕዛዞቻቸው መሠረት በትኩረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ አራት

በዚህ መልመጃ ሥር ቃላትን የሚመለከቱ መልመጃዎች ቀርበዋል። በትዕዛዞቹ መሠረት መልመጃዎቹን ያሠሯቸው። የመልመጃዎቹንም መልሶች በቅድሚያ ተማሪዎች እንዲናገሩ/ እንዲያነቡ ካደረጉ በኋላ ትክክለኛውን መልስ ይንገሯቸው። የማቧደን ተግባራቱንም የሚከተለውን ምሳሌ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያሳዩአቸው።

ለምሳሌ፡- "እህል" የሚል ጥቅል ቃል ቢኖር ስንዴ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ ማሽላ፣... በማለት ልንዘረዝር እንችላለን። (በቢጋር ሠንጠረዡ ውስጥ በማስገባት ያሳዩአቸው።)




(የልብስ ዓይነቶች ባህላዊና ዘመናዊ ልብስ በሚለው ጥቅል ቃል ይከፈላሉ። ለምሳሌ ባህላዊ በሚለው ሥር "ጋቢ" ዘመናዊ በሚለው ሥር ደግሞ "ጂንስ ሱሪ" የሚሉት በመጻፍ ያሳዩአቸው።)

እንዲሁም መልመጃ "ሠ"ን ከማሠራትዎ በፊት ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ ለተማሪዎች ይግለጹላቸው።

# ማስታወሻ

በዚህ የክፍል ደረጃ ስለተዘውታሪ የርባታ ምዕላዶች እናያለን። ተዘውታሪ የምንለው በተደጋጋሚ በቋንቋው ውስጥ የምንገለገልበት ቅርጽ ነው። ለምሳሌ የቃላትን ነጠላና ብዙ ቁጥር ለመለየት የምንጠቀምባቸው የአብገር ምዕላዶች አሉ። ከእዚህም ውስጥ አንዳንዶቹ ተዘውታሪና በበርካታ ቃላት ላይ ሊገኙ ሲችሉ አንዳንዶቹ ደግሞ አልፎ አልፎ የሚገኙ ናቸው። ለምሳሌ "ቤቶች" በሚለው ቃል ላይ የተጨመረው አብገር ምዕላድ /-ኦች/ ተዘውታሪ ሲሆን በአንጻሩ "ካህናት" በሚለው ቃል ላይ ያለው አብገር ምዕላድ /-ኣት/ ተዘውታሪ ያልሆነ ምዕላድ ነው።

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር የወልና የተጸውዖ ስሞችን እንዲለዩ የሚያስችሉ ማስታወሻና መልመጃዎች ቀርበዋል። መልመጃዎቹንም በትዕዛዞቻቸው መሠረት ያሠሯቸው። የመልመጃዎቹንም መልሶች በቅድሚያ ተማሪዎች እንዲናገሩ/እንዲያነቡ ካደረጉ በኋላ ትክክለኛውን መልስ ይንገሯቸው።

በተጨማሪም ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ ለተማሪዎች ይግለጹላቸው። በዚህ የክፍል ደረጃ በመነጠልና በማጣመር ሥር እንደ ዋና ቃል የተወሰደው በራሱ ትርጉም የሚሰጠው ቃል ነው። መነጠልና ማጣመር ማለት አንድን ውስብስብ ቃል ወደተለያዩ ምዕላዶች በመነጠልና በማጣመር የምናነብበት ሂደት ነው። ለምሳሌ "እንደ-ወደድ-ኡ-ት" ተነጣጥሎ ሲነበብ "እንደወደዱት" አጣምረው ሲነበብ ያለውን ልዩነት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፈው ያሳዩአቸው።

## 4. ግምገማ

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መረዳታቸውን በሚከተሉት ነጥቦች ይገምግሙ።

- ተማሪዎች ስለባህላዊ ልብሶች የሚያውቁትን መናገርና መጻፋቸውን ይከታተሉ።
- አያያዥ ቃላትን በትክክል እየተጠቀሙ መናገራቸውን ይከታተሉ።
- ለቃላት ትክክለኛ አውዳዊ ፍቺ መስጠታቸውን ያረጋግጡ።
- ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ መጠቀም መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ቃላትን በትክክል ማቧደን መቻላቸውን ይገምግሙ።
- ቃላትን በትክክል ነጣጥሎና አጣምሮ ማንበብ መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ የርባታ ምዕላዶችን መለየት መቻላቸውን ይገምግሙ።
- መነሻ ሀሳቦችን በመጠቀም ዓረፍተነገር መጻፍ መቻላቸውን ይገምግሙ።
- አቀላጥፈው ማንበብ መቻላቸው ይገምግሙ።
- የወል ስምና የተጸውዖ ስሞችን በተገቢ መንገድ መለየት መቻላቸውን ይከታተሉ።

# የተመረጡ የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ

## መልመጃ አንድ

ሀ. ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት (ከአንድ በላይ መልሶች ሊኖራቸው ይችላል።)

ለምሳሌ፡

1. አንድ ሰው የተወለደበት አካባቢ
2. በቀን ውስጥ አንድ ሰው የሚመገበው ምግበ ሲሆን ቢያንስ ቁርስ፣ ምሳ እና/ወይም እራትን የሚያጠቃልል ነው።

(በዚህ ዓይነት ለሌሎቹ ቃላትና ሀረጋት ተማሪዎቹ አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።)

ለ. የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎች መልሶች

1. የጋሞ ማኅበረሰብ ናቸው።

(በዚህ ዓይነት ሌሎቹን ጥያቄዎች ተማሪዎቹ መልሶችን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሁለት

ሀ. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

1. ባህላዊ ልብስ አንድ ማኅበረሰብ ማንነቱን ለመግለጽና እሴቱን ከትውልድ ወደትውልድ ለማስተላለፍ ይጠቀምበታል።

(በዚህ ዓይነት ሌሎቹን ጥያቄዎች እያነበቡ ተማሪዎቹ መልሶችን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።)

ለ. ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት

(ከአንድ በላይ መልሶች ሊኖራቸው ይችላል።)

## መልመጃ ሦስት

ሀ. ሥርዓተነጥቦችን በተገቢው ቦታ ማስገባት

1. ባህላዊ ልብሶቻችን ዓለማቀፋዊ ተወዳጅነት አግኝተዋል፤ ተፈላጊነታቸውም ጨምሯል።
2. ታዳሚዎች ከመቀመጫቸው ተነስተዋል፤ ጭብጨባው ደምቋል፤ ሙሽሮቹ ወደዳሱ ሳይገቡ አልቀረም።

3. ባህላዊ ልብሶች መቼ መቼ ይለበሳሉ?
4. ባህላዊ ልብሶች ከጥጥ፣ ከበግ ፀጉር፣ ከተልባ እግርና ከቆዳ ይሠራሉ።
5. በችኮላ የተሠራ ሥራ ሁሉ ስህተት አያጣውም።
6. ለምን አረፈድክ?

**ለ. ዓረፍተነገር መሥራት**

(የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ይመሠርታሉ።)

**ሐ. ዓረፍተነገር መሥራት**

(የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ይመሠርታሉ።)

## መልመጃ አራት

**ሀ. ቃላትን በትክክለኛ ቦታ ማስገባት**

1. ኣሻራ
2. ቀለም
3. ውበት
4. ህብር፤ ቀልብ
5. ቁጥር

**ለ. ማቧደን (ከአንድ በላይ መልሶች ሊሰጡ ይችላሉ።)**

**ሐ. (ከአንድ በላይ መልሶች ሊሰጡ ይችላሉ።)**

**መ. እንጀራ፣ ዳቦ፣ ጨጨብሳ፣ ጬምቦ፣ ወዘተ...ሊሉ ይችላሉ።" (እንደየአከባቢያቸው የተለያየ መልስ ሊሰጡ ይችላሉ።)**

**ሠ. ተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ የርባታ ምዕላድ**

1. ተዘውታሪ፡ መኪናዎች፣ በጊቱ፣ ቤቶች፣ ተማሪዎቹ፣ ደብተሬ፣ ልብሳችን፣ አበባዎች፣
2. የተቀሩት ደግሞ ተዘውታሪ ያልሆኑ የርባታ ምዕላዶችን የወሰዱ ናቸው። ለምሳሌ ገዳማት፣ መምህራን፣ ሀረጋት

## መልመጃ አምስት

ሀ. የተጸውዖና የወል ስሞችን መለየት

የወል ስሞች:- ሰው፣ መጽሓፍ፣ መኪና፣ ምግብ፣ ልብስ፣ ተራራ፣ እህል

የተጸውዖ ስሞች:- ጅማ፣ ዱከም፣ ጣና፣ አልማዝ፣ ለሊሴ

ለ. የተለያየ ዓረፍተነገር ሊመሠርቱ ይችላሉ።

ሐ. የሚያውቋቸውን የተለያዩ የወል ስሞችና የተጸውዖ ስሞች ሊዘረዝሩ ይችላሉ።

መ. ነጣጥለውና አጣምረው እንዲያነቡ ያግዟቸው።

# ምዕራፍ ሁለት

## ዝነኛ አትሌቶች (18 ክፍለጊዜ)

### 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- ቃላትን ከምዕላዶች ይለያሉ።
- ምዕላዶችን በማጣመር ቃላት ይመሠርታሉ።
- የተለያዩ ምንባቦችን በማንበብ ዋናውን ሀሳብ ይናገራሉ።
- በክፍል ደረጃው የቀረበ ምንባብ ፍቺን ለመረዳት ድምፀትን በስርዓት ነጥቦች ደረጃ ይጠቀማሉ።
- አንቀጽ ይጽፋሉ።
- ጥቅል ስሞችንና ተውሳከግሶችን ይለያሉ።

### 2. የትምህርት ይዘት

#### 1.1. ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- አትሌት የሚባሉት በየትኛው የስፖርት ዘርፍ እንደሚሳተፉ ሌሎች ሲዘረዝሩ ማዳመጥ፤
- ሌሎች ተማሪዎች ስለሚያውቋቸው አትሌቶች የሕይወት ታሪክ ሲናገሩ ማዳመጥ፤
- መምህሩ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላቸውን ማዳመጥ፤

#### 1.2. ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- በቡድን ተወያይተው መናገር
- ስለሚያውቋቸው አትሌቶች የሕይወት ታሪክ መናገር

#### 1.3. ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

- ለቁልፍ ቃላት የሰጡትን ፍቺ ማንበብ
- ለአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በጽሑፍ የሰጡትን መልስ ማንበብ
- ፋናወጊዋ አትሌት የሚለውን ምንባብ ማንበብ
- ፋናወጊዋ አትሌት የሚለውን ምንባብ ድምጽ በማሰማት በፍጥነትና በትክክል ማንበብ
- ፋናወጊዋ አትሌት የሚለውን ምንባብ በለሆሳስ ሥርዓነጥቦችን ጠብቆ በትክክል ማንበብ

### 1.4. ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- ስለንጽህና አጠባበቅ አጭር አንቀጽ መጻፍ፤
- እንደኮሎኔል አትሌት ደራርቱ ቱሉ በአትሌቲክስ ወይም በሌሎች መስኮች ውጤታማ ለመሆን ምንምን እንደሚያደርጉ አጭር አንቀጽ መጻፍ፤
- ከኮሎኔል አትሌት ደራርቱ ቱሉ የህይወት ታሪክ የተማሩትን ቁምነገር በአንድ አንቀጽ መጻፍ፤

### 1.5. ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ተመሳሳይ ቃላትን መለየት

### 1.6. ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው

- የጊዜ አመልካች ተውሳከግሶችን መጠቀም፤
- ምዕላዶችን ከቃላት መለየት፤
- ምዕላዶችን በማጣመር ቃላት መመሥረት፤
- የጥቅል ስሞችን መለየት፤

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎችንና ብልሃቶችን መጠቀም፤
- ከዝርዝር ወደአጠቃላይ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የማስተማሪያ ስልቶችን መጠቀም፤
- ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል እንዲወያዩ ማመቻቸት፤
- የተለያዩ ቃላት በቻርት በማቅረብ ተመሳሳይ የሆኑትን እንዲለዩ ማበረታታት፤
- የአትሌቶችን ፎቶ በማቅረብ ስማቸውንና የሚሳተፉበትን የስፖርት ዓይነት እንዲናገሩ ማበረታታት፤
- አንድ ተማሪ ንፅህና መጠበቅን በተመለከተ በምልክት ሲገልጽ ሌሎቹ በምልክት የተገለጸውን እንዲገምቱ ማበረታታት፤
- የአንድ ታዋቂ ሰው የሕይወት ታሪክ ምሳሌ በመስጠት መሰል የሕይወት ታሪክ እንዲጽፉ ማገዝ፤
- የተለያዩ የጥቅል ስሞችን በቻርት በማቅረብ ተማሪዎች ለይተው እንዲጽፉ ማለማመድ፤
- እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎችንም መጠቀም ይችላሉ።

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር! በትምህርት አንድ ሥር መነሻ የሚሆኑ የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው፤ የሚሰጧቸውንም ምላሾች እንዳለ ይቀበሏቸው። ተማሪዎቹ የተለያዩ መልሶችን

ሊሰጡ ስለሚችሉ ለማረም መሞከር አያስፈልግም። ምላሾቹን ከተቀበሉ በኋላ ወደዋናው ትምህርት ይግቡ። በመጀመሪያ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው። በመጀመሪያው ንባብ ተማሪዎች በጸጥታ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። በመቀጠል በቦርድ ላይ የተሰጡትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እያዳመጡ መሥራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው። ከዚያም በምንባቡ መሠረት የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው። የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ የሚሠሩት በቀጣይ ክፍለጊዜ ስለሆነ ከማሠራትዎ በፊት ሀሳቡን ለማስታወስ ምንባቡን በድጋሚ ያንብቡላቸው።

## ብርቅዬዋ አትሌት

ሐምሌ 12 ቀን 1975 ዓ.ም በፊንፊኔ ከተማ ተወለደች። ለወላጆቿ አራተኛ ልጅ ናት። ሦስት እህቶችና ሁለት ወንድሞች አሏት። አባቷ አነስተኛ የወር ደመወዝ ነበራቸው። በዚህ የተነሳ በሕፃንነት ዕድሜዋ ከትምህርቷ ጎንለጎን የቤተሰቦቿን ችግር ለማቃለል ብዙ ጥረት አድርጋለች። በዕድሜም ሆነ በአካል እያደገች ስትመጣ በግንባታ ሥራ ውስጥ ተቀጥራ ሠርታለች። ጀሪካን ተሸክማ ውሃ በመቅዳት፣ ወደጫካ እየሄደች ለምግብ ማብሰያ የሚሆን ቅጠል በመልቀም ቤተሰቦቿን ትረዳ ነበር። በአጠቃላይ ኑሮን ለማሸነፍ እጅግ ፈታኝ የሆነ ህይወት አሳልፋለች። ይህች ብርቱ ወጣት አትሌት መሠረት ደፋር ትባላለች።

በዚህ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ያደገችው መሠረት ወደሩጫው ዓለም የገባችው በልጅነት ዕድሜዋ ነበር። የአትሌቲክስ ተሰጥዖዋ ጎልቶ የወጣው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በመከታተል ላይ እያለች ነው። በወቅቱ በትምህርትቤት እና በትምህርት ሚኒስቴር በኩል በሚደረጉ የሩጫ ውድድሮች ትሳተፍ ነበር። በተለይም በ800 ሜትር፣ በ1500 ሜትርና በ3ሺህ ሜትር ርቀቶች ተካፍላ በተደጋጋሚ አሸናፊ ሆነች። ተስፋዋንና ምኞቷን ለማሳካት ከቀድሞው በበለጠ ልምምዷን ማጠናከር ጀመረች።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አትሌት መሠረት ኑሮን ለማሸነፍ ምን ምን ተግባራትን አከናውናለች?
2. የአትሌት መሠረት ተሰጥዖ ጎልቶ የወጣው መቼ ነው?

በዚህም ጊዜ ቢሆን ልዩልዩ ችግሮች ያጋጥሟት ነበር። ችግሮቹን ግን በጽናት ተቋቁማ በልምምድ ላይ እንዳለች ለስኬቷ በር ከፋች የሆነ አጋጣሚ ተፈጠረ። በአዲስ አበባ ስታዲዮም ለአበበ ቢቂላ መታሰቢያ በተዘጋጀ ውድድር ላይ በ5 ሺህ ሜትር ተሳትፋ አሸናፊ ሆነች። ይህንን ብቃቷን ያየው የባንኮች አትሌቲክስ ቡድን ዋና አሰልጣኝ የቡድኑ አባል አደረጋት። የባንክ ቡድኑን ከተቀላቀለች በኋላ በእቅድ ላይ የተመሠረተ ልምምዷን በትጋት አከናወነች። ልምምዷን ከልብ በመነጨ ፍላጎት መሥራቷና ጽናቷ ደግሞ በሀገር ውስጥ ውድድሮች በተከታታይ የአሸናፊነትን ክብር ለመቀዳጀት አበቃት።

ካላት ብቃት አንፃር ብዙም ሳትቆይ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ የአትሌቲክስ ቡድን ተመረጠች። ገና በጧቱ ሀገሯን በሩጫ ለማስጠራት የነበራት ምኞትና ቁርጠኝነት በመሳካቱ ተደሰተች። የመጀመሪያዋ የሆነውን ዓለምአቀፍ ውድድር ለማድረግ ሐምሌ 1991 ዓ.ም. ወደፖላንድ አመራች። በ3 ሺህ ሜትር ርቀት ተወዳድራ ሁለተኛ ወጣች። ይህም በዓለምአቀፍ ውድድር የመጀመሪያው አኩሪ ውጤቷ ሆኖ ተመዘገበላት። ከዚህ በኋላ ሀገሯን በመወከል በበርካታ ውድድሮች ላይ ተሳትፋለች። ሌሎች ኩራት አሸናፊዎችን አስመዝግባለች።

መሠረት በተሳተፈችባቸው በርካታ ዓለምአቀፍ ውድድሮች ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን አዳዲስ የዓለም ምርጥ ሰዓቶችንም (ሪኮርድ) አስመዝግባለች። ለምሳሌ በአሜሪካ ኒውዮርክ ከተማ ግንቦት 26 ቀን 1998 ዓ.ም. በተደረገው የ5 ሺህ ሜትር ውድድር ቀደም ሲል የተመዘገበውን ሰዓት አሻሻለች፤ በዓለም የርቀቱ ሪኮርድ ባለቤትም ለመሆን በቃች። ከአንድ ዓመት በኋላም ጃፓን ላይ በተደረገ ውድድር ቀደም ሲል የያዘችውን ሪኮርድ አሻሽላለች። ጥር 26 ቀን 1999 ዓ.ም. በጀርመን ስቱትጋርት በ3 ሺህ ሜትር የቤት ውስጥ ውድድር ተሳትፋ አዲስ ሪኮርድ አስመዝግባለች። ግንቦት 12 ቀን 1999 ዓ.ም. በአሜሪካ ካሊፎርኒያ የሁለት ማይል ሩጫ ውድድር ተካፍላ ፈጥና በመግባት ሪኮርድ አስመዝግባለች። ቤልጅየም ላይ ይህንኑ ሰዓት በማሻሻሏ ከዓለምአቀፍ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን "የዓመቱ ምርጥ አትሌት" የሚል ማዕረግ አግኝታለች። መሠረት፣ አሁንም ቢሆን የሀገሯ ሰንደቅዓላማ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ በማድረግ ላይ የምትገኝ ብርቅዬ አትሌት ናት።

(ቅዱስ ሀብት በላቸው። 2014። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## መልመጃ አንድ

በመልመጃ አንድ ሁለት የተለያዩ ትእዛዞች ሥር ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ተማሪዎች ባዳመጡት መሠረት በቃል የሚመልሷቸው ጥያቄዎች ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ነው። ጥያቄዎቹን እያነበቡላቸው ተማሪዎቹ በቃል በትዕዛዞቹ መሠረት እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች መልሶቻቸውን በምሳሌ አስደግፈው እንዲመልሱ ያድርጓቸው።

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት በቡድን ውይይት ማድረግ የሚያስችሉ ሀሳቦች ቀርበዋል። ስለዚህ ሀሳቦቹን መሠረት በማድረግ ንግግር እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው።

## ተግባር አንድ

በዚህ ተግባር ሥር ንግግር ለማዳበር የሚረዱ ሁለት ሀሳቦች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ተማሪዎች "ብርቅዬዋ አትሌት" ከሚለው ምንባብ የተገነዘቡትን ቁምነገር በቡድን ተወያይተው

በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲናገሩ የሚጠይቅ ነው። ሁለተኛው ተግባር ደግሞ ተማሪዎች ስለሚያውቋቸው ሌሎች አትሌቶች የሕይወት ታሪክ ሰው በመጠየቅ ወይም መጽሐፍ በማንበብ በንግግር እንዲናገሩ የሚጠይቅ ነው። ስለዚህ ተግባሩን በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ያሠሯቸው።

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር "ፋናወጊዋ አትሌት" የሚል ምንባብ ቀርቧል። ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ የቅድመንባብ ጥያቄዎች ተሰጥቷል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸውና እንዲመልሱ ያነሳሷቸው፤ የሚሰጡትንም መልሶች ይቀበሏቸው። ከዚያም ተማሪዎች ምንባቡን ሲያነቡ ከአንደኛው አንቀጽ ጀምረው በየአንቀጾቹ መጨረሻ ቆም እያሉና የአንቀጾችን መልዕክት እያጠቃለሉ እንዲያነቡ ያድርጉ። ያልተረዱት አንቀጽ ሲኖር በድጋሜ በማንበብ ለመገንዘብ እንዲሞክሩ ይንገሯቸው። ከዚያም በምንባቡ ላይ ተመሥርተው የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሁለት

በመልመጃ ሁለት በሁለት የተለያዩ ትእዛዞች ሥር ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ተማሪዎች ባነበቡት ምንባብ መሠረት በጽሑፍ መልስ የሚሰጡበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ባዶ ቦታን በተገቢ ቃላት እንዲያሟሉ የሚጠይቁ ናቸው። ተማሪዎቹ የጥያቄዎቹን ትዕዛዞች እየተከተሉ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች መልሶቻቸውን በምሳሌ አስደግፈው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ግብረምልስም ይስጧቸው።

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ተግባር ሥር አጫጭር አንቀጾችን ለመጻፍ የሚያስችል ተግባራት ቀርበዋል። በመሆኑም ለተግባራቱ በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።

## ተግባር ሦስት

በዚህ ተግባር ሥር ሦስት የተለያዩ ትዕዛዞች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ሰዎች ንጽህናን ለመጠበቅ የት እንደሚሄዱና ምን እንደሚያደርጉ የሚገልጽ አንድ አንቀጽ ጽፈው እንዲያነቡ የሚጠይቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ እንደኮሎኔል አትሌት ደራርቱ ቱሉ በአትሌቲክስ ወይም በሌሎች መስኮች ውጤታማ ለመሆን ምንምን እንደሚያደርጉ ጽፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ነው። ሦስተኛው ከኮሎኔል አትሌት ደራርቱ ቱሉ የህይወት ታሪክ የተማሩትን ቁምነገር በአንድ አንቀጽ እንዲጽፉ የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም የቀረቡላቸውን ተግባራት በተሰጣቸው ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ሥር ተመሳሳይ ቃላትን እንዲለዩ የሚያስችል መልመጃ ቀርቧል። ስለዚህ በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሦስት

በዚህ መልመጃ ሥር በፍቺ ተያያዥ የሆኑ ቃላትን ለይተው በየምድባቸው እንዲያስቀምጡ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ስለሆነም በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር የጊዜ ተውሳከግሶችንና የጥቅል ስሞችን በዓረፍተነገር ውስጥ እንዲለዩ የሚረዳችሁ ማስታወሻ፣ ተግባራትና መልመጃዎች ተካተዋል። ስለሆነም የቀረቡላትን መልመጃዎችና ተግባራት በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።

## ተግባር አራት

በዚህ ተግባር ሥር አንድ ተማሪ ንፅህና መጠበቅን በተመለከተ በምልክት ሲገልጽ ሌሎች ደግሞ ድርጊቱን ገምተው በተለያዩ ጊዜያት ከፋፍለው ዓረፍተነገር እንዲመሠርቱ የሚጠይቅ ነው። ስለዚህ በትዕዛዙ መሠረት ተማሪዎቹን ያሠሯቸው፤ ለሥራቸውም ግብረመልስ በመስጠት ያበረታቷቸው።

## መልመጃ አራት

በዚህ መልመጃ ሥር ከቃላት ውስጥ ቅጥያ ምዕላዶቻቸውን ለይተው የሚመልሱበት ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመልመጃዎቹንም መልሶች በቅድሚያ ተማሪዎች እንዲናገሩ ወይም እንዲያነቡ ካደረጉ በኋላ ትክክለኛዎቹን መልሶች በጥቁር ሠሌዳ ላይ በመጻፍ ያሳዩአቸው።

## መልመጃ አምስት

በዚህ መልመጃ ሥር ደግሞ ምዕላዶቻችን በማጣመር ቃላት የሚመሠርቱባቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመልመጃዎቹንም መልሶች በቅድሚያ ተማሪዎች እንዲናገሩ ወይም እንዲያነቡ ካደረጉ በኋላ ትክክለኛዎቹን መልሶች በጥቁር ሠሌዳ ላይ በመጻፍ ያሳዩአቸው።

## መልመጃ ስድስት

በዚህ መልመጃ ሥር ጥቅል ስሞችን ለይተው የሚመልሷቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመልመጃዎቹንም መልሶች በቅድሚያ ተማሪዎች እንዲናገሩ ወይም እንዲያነቡ ካደረጉ በኋላ ትክክለኛዎቹን መልሶች ይንገሯቸው።

### 1. ግምገማ

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መረዳታቸውን በሚከተሉት ነጥቦች ይገምግሙ።

- ተማሪዎች ስለታዋቂ አትሌቶች የሚያውቁትን መናገርና መጻፋቸውን ይከታተሉ።
- በቡድን ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ መናገር መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- አጭር አንቀጽ መጻፍ መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ምዕላድን ከቃላት መለየት መቻላቸውን ይገምግሙ።
- ተመሳሳይ ቃላትን መለየት መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- የጥቅል ስሞችን መለየት መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- የጊዜ አመልካች ተውሳከግሶችን በዓረፍተነገር መጠቀም መቻላቸውን ያረጋግጡ።

## የተመረጡ የመልመጃ ጥያቄዎች  መልስ

## መልመጃ አንድ

ሀ. የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች መልሶች

1. ፖላንድ
2. በአሜሪካ ኒውዮርክ፣ በጃፓን።

(በዚህ ዓይነት ለሌሎቹ መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።)

ለ. ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት

1. ተመድባ (ደመወዝ እየተከፈላት መሥራት መጀመሯን ያሳያል)
2. ክብረወሰን ማሻሻል

(በዚህ ዓይነት ሌሎቹን ጥያቄዎች ተማሪዎቹ መልሶችን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሁለት

ሀ. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መልሶች

1. ለኢትዮጵያም ሆነ ለአፍሪካ የመጀመሪያ አትሌት ስለሆነች

2. ከብት እያገደች፣ እህል እየፈጨችና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎችን በመሥራት

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## ለ. ባዶ ቦታ በተገቢ ቃላት መሙላት

1. በ1993
2. በስድስት ኪሎ ሜትር]

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሦስት

በፍቺ ተያያዥ የሆኑ ቃላትን መለየት

1. ማጋራት
2. አያሌ፣ ብዙ፣
3. መከላከል፣ ማገድ፣

## መልመጃ አራት

### ሀ. ቅጥያ ምዕላዶችን ከቃላት መለየት

| | ቃላት | ምዕላዶች |
|---|---|---|
| 1 | ሰውነት | ሰው-ነት |
| 2 | ልጆች | ልጅ-ኦች |
| 3 | ቀልደኛ | ቀልድ-ኧኛ |

(ሌሎቹን ቃላት በዚህ ዓይነት እንዲሠሩ ያድርጉ። ግብረምልስም ይሰጧቸው።)

ለ. ምዕላዶችን በማጣመር ቃላት መመስረት

## መልመጃ አምስት

1. ሰንደቅ-ዓላማ-ኣችን የሚለውን ስናጣምር ሰንደቃላማችን ይሆናል።
2. የስኬታማነታቸው
3. ተወዳጅነትንም
4. አትሌቶቻችን
5. ሊያጋጥሟቸው
6. የብዙዎቻችን
7. ተተኪዎችን

(ሌሎቹንም በዚህ ዓይነት እንዲሠሩ ያድርጉ። ግብረምልስም ይሰጧቸው።)

ሐ. ተመሳሳይ ቃላትን ለይቶ

## መልመጃ ስድስት

ሀ. ጥቅል ስሞችን መለየት

ጥቅል ስሞች፡- እህል፣ ጸጉር

ለ. ጻፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጥራጥሬ | ቤት | ፍራፍሬ | የዱር እንስሳት |
| ለምሳሌ፡ አተር | ሳሎን | ሙዝ | ጥንቸል |
| ባቄላ | መኝታ | ብርቱካን | ሚዳቋ |
| ሽምብራ | ባኞ | ፓፓያ | አንበሳ |
| አኩሪ አተር | ወጥቤት፣ ወዘተ | ማንጎ፣ ወዘተ | ጅብ፣ ወዘተ |

# ምዕራፍ ሦስት

## ቃላዊ ግጥሞች (18 ክፍለጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- አዳዲስ የተማሩትን ቃላት አዳምጠው ጥቅም ላይ ያውላሉ፤
- ግጥምን አቀላጥፈው ያነባሉ፤
- ግጥምን ይጽፋሉ፤
- በዓረፍተነገሮች ውስጥ ቅንፍና ህዝባርን ይጠቀማሉ፤
- የተማሩትን አዳዲስ ቃላት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቧቸው ቃላዊ ግጥሞች ውስጥ ይጠቀማሉ፤
- የጊዜ ተውሳከግሶችን ትለያላችሁ፤
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- ስዕል ተመልክተው ሌሎች ተማሪዎች የተረዱትን ሲናገሩ ማዳመጥ፤
- ሌሎች ተማሪዎች ስለሚያውቋቸው የሥራ ግጥሞች ሲናገሩ ማዳመጥ፤
- መምህሩ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላቸውን የሥራ ቃላዊ ግጥም ማዳመጥ፤

### 2.2. ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- በቡድን ተወያይተው መናገር
- በአካባቢያቸው በእርሻ፣ በአጨዳ፣ በውቂያ ላይ የሚገጠሙ ቃላዊ ግጥሞችን መናገር

### 2.1. ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

- የሚያውቋቸውን ቃላዊ ግጥሞች ማንበብ
- ለቁልፍ ቃላት የሰጡትን ፍቺ ማንበብ
- “የእርሻ ጊዜ ቃላዊ ግጥም” የሚለውን ቃላዊ ግጥም ማንበብ
- “የእርሻ ጊዜ ቃላዊ ግጥም” የሚለውን ቃላዊ ግጥም ዜማዊ ቃናቸውን በመጠበቅ ማንበብ
- የግጥም አነባብ ስልቶችን በመጠቀም “የፍቅር ቃላዊ ግጥሞች” የሚለውን ቃላዊ ግጥም ማንበብ

## 2.1. ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- የግጥም ሀረጋትን በትክክለኛ አሰዳደር በማደረጃት አስተካክሎ መጻፍ፤
- የግጥሞችን ጭብጦች በሦስት ዓረፍተነገር መጻፍ፤
- በትምህርት፣ በእርሻ፣ በሠርግ፣ በአጨዳ፣ ወይም በውቂያ ላይ ከሚገጠሙ ቃላዊ ግጥሞች በመምረጥ ቃላዊ ግጥም መጻፍ፤

## 2.1. ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ተቃራኒ ቃላትን መለየት
- የቃላትን ትክክለኛ ተቃራኒ ፍቺ ማዛመድ

## 2.1. ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው

- የጊዜ ተውሳከግሶችን መለየት፤
- ምዕላዶችን ከቃላት መለየት፤
- የጊዜ አመልካች ተውሳከግሶችን መጠቀም፤
- ህዝባር ወይም ቅንፍ መጠቀም፤

# 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎችንና ብልሃቶችን መጠቀም፤
- ከዝርዝር ወደአጠቃላይ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የማስተማሪያ ስልቶችን መጠቀም፤
- ተማሪዎችን በቡድን በማከፋፈል እንዲወያዩ ማመቻቸት፤
- የተለያዩ ቃላት በቻርት በማቅረብ ተቃራኒ የሆኑትን እንዲለዩ ማበረታታት፤
- ቃላዊ ግጥሞችን በመቅረጸ ድምፅ በመቅዳት ተማሪዎቹን ማሰማት፤
- ቃላዊ ግጥሞችን በማዜም እንዲያቀርቡ ማድረግ፤
- እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎችንም መጠቀም ይችላሉ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር! በዚህ ትምህርት ሥር ለማዳመጥ መነሻ የሚሆኑ የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው፤ የሚሰጧቸውንም ምላሾች እንዳለ ይቀበሏቸው። ተማሪዎቹ የተለያዩ መልሶችን ሊሰጡ ስለሚችሉ ለማረም መሞከር አያስፈልግም። ምላሾቹን ከተቀበሉ በኋላ ወደዋናው ትምህርት ይግቡ። በመጀመሪያ ቀጥሎ የቀረበውን ቃላዊ ግጥም ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው። በመጀመሪያው ንባብ ተማሪዎች በጸጥታ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። በመቀጠል በቦርድ ላይ የተሰጡትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እያዳመጡ መሥራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው። ከዚያም በቃላዊ ግጥሙ መሠረት የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም

ይስጧቸው። የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በቀጣይ ክፍለጊዜ የሚሠሩ ስለሆነ ከማሠራትዎ በፊት ሀሳቡን ለማስታወስ ግጥሙን በድጋሚ ያንብቡላቸው።

# የአጨዳ ጊዜ

የኀበዝ ማጭድ ታስታውቃለች፣
እንዳዘንተኛ ፊቷን ፊጅታለች፣
እራሷን ታማ ሻሽ ጠምጥማለች።
ሳብ አልቢኑን፤
ማጨጃውን።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አዳዲስ ቃላትና ሐረጋትን በመለየት በደብተራችሁ ላይ ጻፉና ጥንድ ጥንድ በመሆን በፍቺያቸው ላይ ተወያዩ።
2. ሻሽ የጠመጠመች ማጭድ ሲል ምን ለመግለጽ ይመስላችኋል?

ላሽማጭዴ ጉረሻ ሆዴ፣
ማጭዴ ጉረሻ ሆዴ።
ማጭዴ ስለት ቅጠለ በላ፣
ቆርጦ አስቀማጭ ክንዱ እስኪ ላላ።
(ዘሪሁን፣ 2002፣ 49)

## መልመጃ አንድ

በመልመጃ አንድ ሥር የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ስለዚህ ጥያቄዎቹን ተማሪዎቹ በጽሑፍ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች መልሶቻቸውን በምሳሌ አስደግፈው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት በቡድን ውይይት ማድረግ የሚያስችላቸው ሀሳብ ቀርቧል። ስለዚህ ሀሳቡን መሠረት በማድረግ ንግግር እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው።

## ተግባር አንድ

በዚህ ተግባር ሥር ንግግር ለማዳበር የሚረዳው ሀሳብ ቀርቧል። ይኸውም ተማሪዎች በእርሻ፣ በአጨዳ፣ በውቂያ ላይ የሚገጠሙ ቃላዊ ግጥሞችን ላይ በቡድን ተወያይተው በቃል እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ነው። ስለዚህ ተግባሩን በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ያሠሯቸው።

# ትምህርት ሦስት፥ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር "የእርሻ ጊዜ ቃላዊ ግጥም" የሚል ቃላዊ ግጥም ቀርቧል። ተማሪዎች ቃላዊ ግጥሙን እንዲያነቡ የቅድመንባብ ጥያቄዎች ተሰጥቷል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸውና እንዲመልሱ ያነሳሷቸው፤ የሚሰጡትንም መልሶች ይቀበሏቸው። ከዚያም ተማሪዎች ቃላዊ ግጥሙ ላይ ተመሥርተው የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሁለት

በመልመጃ ሁለት በሁለት የተለያዩ ትእዛዞች ሥር ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ተማሪዎች ባነበቡት ቃላዊ ግጥም መሠረት በቃል መልስ የሚሰጡበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በቃላዊ ግጥሙ መሠረት ለቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ነው። ተማሪዎቹ የጥያቄዎቹን ትዕዛዞች እየተከተሉ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች መልሶቻቸውን በምሳሌ አስደግፈው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ግብረምልስም ይስጧቸው።

## ተግባር ሁለት

በዚህ ተግባር ሥር አቀላጥፎ ማንበብን የሚያለማምዷቸው ሁለት የተለያዩ ትዕዛዞች ቀርበዋል። የመጀመሪያው በማስታወሻው መሠረት በሚሰጣቸው የግጥም አነባበብ ስልት መሠረት "የእርሻ ጊዜ ቃላዊ ግጥሞች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ቃላዊ ግጥም ዜማዊ ቃናቸውን በመጠበቅ በየተራ እንዲያነቡ የሚጠይቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የግጥም አነባበብ ስልቶችን በመጠቀም "የፍቅር ቃላዊ ግጥሞች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ግጥም በግላቸው ድምጽ እያሰሙ እንዲያነቡ የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም የቀረቡላቸውን ተግባራት በተሰጣቸው ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት አራት፥ መጻፍ

በዚህ ተግባር ሥር ግጥም ለመጻፍ የሚያስችል መልመጃና ተግባራት ቀርበዋል። በመሆኑም ለተግባራቱ በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።

### መልመጃ ሦስት

በዚህ መልጃ ሥር የግጥም ሐረጋትን በትክክለኛ አሰዳደር በማደራጀት ግጥሙን አስተካክለው እንዲጽፉ የሚጠይቅ ጥያቄ ቀርቧል። ስለሆነም በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይሥጧቸው።

## ተግባር ሦስት

በዚህ ተግባር ሥር ሦስት የተለያዩ ትዕዛዞች ቀርበዋል። ሁለቱ የጻፏችኋቸውን ግጥሞች ጭብጣቸውን በሦስት ዓረፍተነገር ጽፈው ለክፍል ጓደኞቻችሁ እንዲያነቡ የሚጠይቅ ሲሆን የቀረው ደግሞ በትምህርት፣ በእርሻ፣ በሠርግ፣ በአጨዳ፣ ወይም በውቂያ ላይ ከሚገጠሙ ቃላዊ ግጥሞች አንድ መርጠው የራሳቸውን ባለአራት ስንኝ ቃላዊ ግጥም ጽፈው በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻቸው እንዲያነቡ የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም የቀረቡላቸውን ተግባራት በተሰጣቸው ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ሥር የቃላትን ተቃራኒ ፍቺ እንዲለዩ የሚያስችል መልመጃ ቀርቧል። ስለዚህ በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው።

### መልመጃ አራት

በዚህ መልመጃ ሥር ሁለት ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው ከቀረቡት ቃላት ውስጥ ተቃራኒ የሆኑትን ለይተው እንዲያወጡ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው በፍቺ ተቃራኒ የሆኑ ቃላትን እንዲያዛምድ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ስለሆነም በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር የጊዜ ተውሳከግሶችን በዓረፍተነገር ውስጥ እንዲለዩ የሚረዳቸው ማስታወሻና መልመጃዎች ተካተዋል። እንዲሁም ህዝባርና ቅንፍ በመጠቀም ዓረፍተነገር መመስረት ቀርቧል። ስለሆነም የቀረቡትን መልመጃዎች በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።

### መልመጃ አምስት

በዚህ መልመጃ ሥር ሦስት የተለያዩ ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው የጊዜ አመልካች ተውሳከግስ

የሆኑትን ቃላትና ሐረጋት ከዓረፍተነገር ውስጥ ለይተው እንዲጽፉ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የግዜ አመልካች ተውሳከግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገር እንዲጽፉ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ናቸው። ሦስተኛው ህዝባርና ቅንፍ በመጠቀም ዓረፍተነገር እንዲመሠርቱ የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም በትዕዛዞቻቸው መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## ግምገማ

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መረዳታቸውን በሚከተሉት ነጥቦች ይገምግሙ።

- ተማሪዎች የሚያውቁትን ቃላዊ ግጥሞች በማዜም ማቅረባቸውን ይከታተሉ።
- በቡድን ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ መናገር መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ተውሳከግሶችን መለየት መቻላቸውን ይገምግሙ።
- ህዝባርና ቅንፍ በትክክል መጠቀም መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- የጊዜ አመልካች ተውሳከግሶችን በዓረፍተነገር መጠቀም መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ቃላዊ ግጥም መጻፍ መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ግጥምን በትክክል ማንበብ መቻላቸውን ያረጋግጡ።

# የተመረጡ የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ

## መልመጃ አንድ

1. ሻሽ የጠመጠመች ናት።
(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሁለት

### ሀ. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

1. በግጥሙ መሠረት የተለያየ መልስ ሊሰጡ ይችላሉ።
(ቀሪውን ጥያቄ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

### ለ. ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት

1. ወፍ፣ ዝንጀሮ፣ ወይም ጦጣ ሰብል እንዳይበሉ ለመከላከል የድንጋይ መሸከሚያ ኪስ ያለው ከገመድ የሚሠራ ባህላዊ መሣሪያ ነው።

2. ሥልጣን ማግኘት

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሦስት

የግጥም ሐረጋትን በትክክለኛ አሰዳደር በማደራጀት አስተካክሎ መጻፍ

1. ተላላው ገበሬ ይውላል ከጥላ፣
   ውርጭ የመሰለ ብር ከመሬት ሲፈላ።
2. አላየኸውም ወይ የምስሩን ተራ፣
   እንደክረምት አግቢ ሺልንጉ ሲፈላ።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ አራት

**ሀ. ተቃራኒ የሆኑ ቃላት መለየት**

- ድጋፍ፤ ተቃውሞ
- በፊት፤ በኋላ
- ፍቅር፤ ጥላቻ
- ጠቀሜታ፤ ጉዳት

(ሌሎቹንም በዚህ ዓይነት እንዲሠሩ ያድርጉ። ግብረምልስም ይሰጧቸው።)

**ለ. አዛምድ**

1. ሐ
2. ሠ
3. ሀ
4. መ
5. ረ

## መልመጃ አምስት

**ሀ. የጊዜ አመልካች ተውሳከግስ የሆኑትን ቃላትና ሐረጋት መለየት**

1. አሁን
2. ቶሎ
3. ዛሬ
4. ዛሬ ማታ
5. ዝናቡ ሳይመጣ፤ በጧት

**ለ. ዓረፍተነገር መመሥረት (የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)**

**ሐ. ዓረፍተነገር መመሥረት (የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)**

# ምዕራፍ አራት

## ዘመናዊ ግብርና (18 ክፍለጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- ጽሑፍን አዳምጠው ቃላዊ ምላሽ ይሰጣሉ፤
- አመዛዛኝ አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- ጊዜ አመልካች ተውሳከ ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገር ይመሠርታሉ፤
- የቃላት ፍቺ ለመስጠት አብሮ ሂያጅ ቃላትን ይጠቀማሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 1.1. ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- በሀገራችን ስለሚካሄደው ግብርና ሌሎች ተማሪዎች ሲናገሩ ማዳመጥ፤
- ሌሎች ተማሪዎች በግብርና ሥራዎቻችን መሻሻል የሚገባቸው ነገሮች ሲናገሩ ማዳመጥ፤
- መምህሩ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላቸውን ምንባብ ማዳመጥ፤

### 1.2. ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- በቡድን ተወያይተው መናገር
- የጽሑፍ አዳምጠው ዋና መልዕክቱን መናገር

### 1.3. ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

- ለቁልፍ ቃላት የሰጡትን ፍቺ ማንበብ
- “ውጤታማ የስንዴ አመራረት” የሚለውን ምንባብ ማንበብ

### 1.4. ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- አመዛዛኝ አንቀጽ መጻፍ፤

### 1.5. ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- አብሮ ሂያጅ ቃላትን መጠቀም

### 1.6. ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው

- የጊዜ ተውሳከግሶችን መለየት፤

## 2. የማስተማሪያ ዘዴ

- ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎችንና ብልሃቶችን መጠቀም፤
- ከዝርዝር ወደአጠቃላይ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የማስተማሪያ ስልቶችን መጠቀም፤
- ተማሪዎችን በቡድን በማከፋፈል እንዲወያዩ ማመቻቸት፤
- የተለያዩ ቃላት በቻርት በማቅረብ አብሮ ሂያጅ የሆኑትን እንዲለዩ ማለማመድ፤
- ዘመናዊ የግብርና እና ባህላዊ ግብርናን እንዲያነጻጽሩ የቪዲዮ ወይም የፎቶ ምስሎችን ማሳየት፤
- አመዛዛኝ አንቀጽ እንዲጽፉ ሞዴል አንቀጽ ወደክፍል በማምጣት በምሳሌው መሠረት እንዲጽፉ ማድረግ፤
- እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎችንም መጠቀም ይችላሉ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር! በዚህ ትምህርት ሥር ለማዳመጥ መነሻ የሚሆኑ የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው፤ የሚሰጧቸውንም ምላሾች እንዳለ ይቀበሏቸው። ተማሪዎቹ የተለያዩ መልሶችን ሊሰጡ ስለሚችሉ ለማረም መሞከር አያስፈልግም። ምላሾቹን ከተቀበሉ በኋላ ወደዋናው ትምህርት ይግቡ። በመጀመሪያ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው። በመጀመሪያው ንባብ ተማሪዎች በጸጥታ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። በመቀጠል በቦርድ ላይ የተሰጡትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እያዳመጡ መሥራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው። ከዚያም ባዳመጡት ምንባብ መሠረት የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዞቻቸው መሠረት ያሠሯቸው። የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በቀጣይ ክፍለጊዜ የሚሠሩ ስለሆነ ከማሠራትዎ በፊት ሀሳቡን ለማስታወስ ምንባቡን በድጋሚ ያንብቡላቸው።

## ግብርና በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ተስማሚ የሆነ የአየር ንብረት ያላት ሀገር ናት። በአየር ንብረቱ የተለያዩ አዝርእትን፣ ፍራፍሬዎችንና ለምግብ የሚውሉ ቅጠላ ቅጠሎችን ማምረት ይቻላል። ይሁን እንጂ በምዕራባዊያን ለብዙ አመታት ስንረዳ ቆይተናል። አሁንም ከእርዳታ ተላቅቀናል ማለት አይቻልም። ለችግሩም በርካታ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። ከእነዚህም መካከል የሥራ ባህላችን ደካማ መሆን፣ ምርጥ ዘሮችን አለመጠቀም፣ መስኖ እርሻና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አለመጠቀማችን ዋነኞቹ ናቸው።

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ያጋጠሟችሁን አዳዲስ ቃላትና ሐረጋት በመለየት በደብተራችሁ ላይ ጻፉና በፍቺያው ላይ ተወያዩ።
2. ባዳመጣችሁት መሠረት ደካማ የሥራ ባህል እንዳለን የሚያመለክቱ ጉዳዮችን ምንምን እንደሆኑ ተናገሩ።

ከዚህም ሌላ ያለን ደካማ የሥራ ባህል ሀገሪቱ ተፈጥሮ የቸራትን ጸጋ በአግባቡ እንዳንጠቀም አድርጎናል። የሚሠሩ እጆች፣ የሚዘሩ ዘሮች፣ የሚታረሱ ለም መሬቶች ይዘን ጠባቂና ኋላቀር ሆነናል። ባለመሥራታችን ብቻ ለበርካታ ዘመናት ስንቸገርና ለድህነት ተጋልጠን ስንራብ ኖረናል። ይህ ብቻም አይደለም፤ ኅብረተሰባችን በዚህ በ21ኛው ክፍለዘመን ውስጥም ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎችን አይጠቀምም። ዛሬም በሬ ወይም የጋማ ከብቶች እየጠመደ ያርሳል። በእንደዚህ ዓይነት ዘዴ ደግሞ ብዙና ሰፋፊ እርሻ ማረስ አይቻልም። ምርጥ ዘርና የማደበሪያ አጠቃቀም ባህሉም ዝቅተኛ ነው። በርግጥ ለነዚህ ችግሮች የሚጠቀሱ ምክንያቶች ቢኖሩም ምርታማነትን ከመቀነስ ረገድ የአንበሳውን ድርሻ ይጫወታሉ። ስለዚህ ቀጣዩ ትውልድ ችግሮቹን ለመቅረፍና ሀገሪቱ የምትታወቅበትን ርሃብ ለማስወገድ ሌትተቀን መሥራት ይኖርበታል። አያቶቹ ያስረከቡትን ሀገር እንዳለች ለልጆቹ ማስተላለፍ የለበትም።

### መልመጃ አንድ

በመልመጃ አንድ ሥር የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ስለዚህ ጥያቄዎቹን ተማሪዎቹ በቃል እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች መልሶቻቸውን በምሳሌ አስደግፈው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት በቡድን ውይይት ማድረግ የሚያስችላቸው ሀሳብ ቀርቧል። ስለዚህ ሀሳቡን መሠረት በማድረግ ንግግር እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው።

### ተግባር አንድ

በዚህ ተግባር ሥር ንግግር ለማዳበር የሚረዳው ሀሳብ ቀርቧል። ይኸውም ተማሪዎች “ግብርና በኢትዮጵያ” በሚል ርዕስ የተነበበላቸው ጽሑፍ ዋና መልዕክቱ ምን እንደሆነ በቡድን ተወያይተውበት በቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር "ውጤታማ የስንዴ አመራረት" የሚል ምንባብ ቀርቧል። ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ የቅድመንባብ ጥያቄዎች ተሰጥቷል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸውና እንዲመልሱ ያነሳሷቸው፤ የሚሰጡትንም መልሶች ይቀበሏቸው። ከዚያም ተማሪዎች ምንባቡ ላይ ተመሥርተው የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሁለት

በመልመጃ ሁለት ሥር በአራት የተለያዩ ትእዛዞች ሥር ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ተማሪዎች ባነበቡት ምንባብ መሠረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት ምክንያት እየሰጡ በቃል መልስ የሚሰጡበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በምንባቡ መሠረት ለተጠየቁት ጥያቄዎች በጽሑፍ መልስ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ነው። ሦስተኛው ደግሞ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት ሲሆን አራተኛው በተሠጠው ምሳሌ መነሻነት የቃላትን ቅርጽ መቀያየር ነው። ተማሪዎቹ የጥያቄዎቹን ትዕዛዞች እየተከተሉ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች መልሶቻቸውን በምሳሌ አስደግፈው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ግብረምልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ተግባር ሥር አመዛዛኝ አንቀጽ ለመጻፍ የሚያስችል ማስታወሻ፣ መልመጃና ተግባራት ቀርበዋል። በመሆኑም ለተግባራቱ በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።

## ተግባር ሁለት

በዚህ ተግባር ሥር ሦስት የተለያዩ ትዕዛዞች ቀርበዋል። ሦስቱም በተለያ ርዕሰ ጉዳይ ላይ አመዛዛኝ አንቀጽ እንዲጽፉ የሚጠይቁ ናቸው። በመሆኑም የቀረቡላቸውን ተግባራት በተሰጣቸው ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው፤ በተሰጣቸው ማስታወሻ መሠረት ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ሥር አብሮ ሂያጅ ቃላትን መጠቀም የሚያስችል መልመጃ ቀርቧል። ስለዚህ በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሁለት

በዚህ መልመጃ ሥር ሦስት ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው ከቀረቡት አማራጮች አብሮ ሂያጅ ቃላትን እንዲመርጡ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ባዶ ቦታ በመሙላት የሚመለሱ ጥያቄዎች ናቸው። ሦስተኛው ደግሞ ተማሪዎቹ አብሮ ሂያጅ ቃላትን ጽፈው ለመምህራቸው እንዲያሳዩ ይጠይቃል። ስለሆነም በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር የጊዜ ተውሳከግሶችን እንዲለዩ የሚረዳቸው ተግባራትና መልመጃዎች ቀርበዋል። እንዲሁም ህዝባርና ቅንፍ በመጠቀም ዓረፍተነገር መመስረት ቀርቧል። ስለሆነም የቀረቡትን መልመጃዎች በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሦስት

በዚህ መልመጃ ሥር ሁለት የተለያዩ ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው የጊዜ አመልካች ተውሳከግስ የሆኑትን ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገር እንዲመሠርቱ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የግዜ አመልካች ተውሳከግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገር እንዲጽፉ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ናቸው። ስለሆነም በትዕዛዞቻቸው መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

### 4. ግምገማ

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መረዳታቸውን በሚከተሉት ነጥቦች ይገምግሙ።

- በቡድን ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ መናገር መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- አብሮ ሂያጅ የሆኑ ቃላትን መለየት መቻላቸውን ይገምግሙ።
- የጊዜ አመልካች ተውሳከግሶችን በዓረፍተነገር መጠቀም መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- አመዛዛኝ አንቀጽ መጻፍ መቻላቸውን ያረጋግጡ።

## የተመረጡ የመልመጃ ጥያቄዎች  መልስ

## መልመጃ አንድ

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

1. “ደካማ የሥራ ባህል” ሲባል እንደማኅበረሰብ ያለው የሥራ ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆንና የሥራ ፍላጎት እምብዛም አለመኖርን ያመለክታል።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሁለት

### ሀ. እውነት ወይም ሀሰት

1. ሀሰት 2. ሀሰት

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።)

### ለ. በጽሑፍ የሚመለስ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

1. ስንዴ በኢትዮጵያ ደጋ እና ወይናደጋ የአየር ንብረት በብዛት ይመረታል።

2. አረም የሰብሉን ቦታ፣ የፀሓይ ብርሃን፣ ውኃና አየር እንዲሁም የምግብ ንጥረ ነገሮችን ይሻማሉ። በተጨማሪም በሰብል ላይ አላስፈላጊ የሆነ ጎጂ ንጥረነገሮችን በሥሮቻቸው አማካኝነት በመልቀቅ ዕድገታቸውን ይገታሉ።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።)

**ሐ. ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት**

1. ማለቅ
2. መርጨት፣ ማሰራጨት

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።)

**መ. በተሰጠው ምሳሌ መሠረት የሚሠሩ**

1. ፈራረሰ፣ ፍርስራሽ፣ መፈራረስ፤
2. ተነጋገረ፣ ተናጋሪ፣ መነጋገር፤

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሦስት

**ሀ. ምርጫ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | መ | 3. | መ |
| 2. | ሀ | 4. | ለ |

**ለ. ባዶ ቦታ መሙላት**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | ገፈት | 6. | ሙጭሊት |
| 2. | ይጣላል | 7. | ግልገል |
| 3. | አተላ | 8. | ያናፋል |
| 4. | ይቆላል | 9. | ያገሳል |
| 5. | ይቃማል | 10. | እንቁላል ጣለች፤ ጫጩት ፈለፈለች |

**ሐ. የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊጽፉ ይችላሉ።**

# መልመጃ አራት

ሀ. የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊጽፉ ይችላሉ።

ለ. የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊጽፉ ይችላሉ።

# ምዕራፍ አምስት

## ቱሪዝም (18 ክፍለጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- አዳምጠው ቃላትን ወደ ምዕላዶች መነጣጠልን ይተገብራሉ፤
- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ሀላፊ ጊዜን በመጠቀም አንቀፅ ይጽፋሉ፤
- ድህረ ቅጥያዎችን ይጠቀማሉ፤
- የተዘጋጀን ፅሑፍ ለመረዳት ራስመር ብልሃቶችን ይጠቀማሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- ሌሎች ተማሪዎች ስለሚያቋቸው የቱሪስት መስህቦች ሲናገሩ ማዳመጥ፤
- ሌሎች ተማሪዎች ስለወንጪ ሐይቅ የሚያውቁትን ሲናገሩ ማዳመጥ፤
- መምህሩ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላቸውን ምንባብ ማዳመጥ፤

### 2.2. ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- ተዘጋጅተው መናገር

### 2.3. ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

- ለቁልፍ ቃላት የሰጡትን አውዳዊ ፍቺ ማንበብ
- "የነጭ ሣር ፓርክ" የሚለውን ምንባብ ማንበብ

### 2.4. ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- ሀላፊ ጊዜን በመጠቀም አንቀጽ መጻፍ፤

### 2.5. ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መለየት

### 2.6. ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው

- ድኅረአምድ ቅጥያዎችን መለየት፤

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎችንና ብልሃቶችን መጠቀም፤
- ከዝርዝር ወደአጠቃላይ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የማስተማሪያ ስልቶችን መጠቀም፤
- ተማሪዎችን በቡድን በማከፋፈል እንዲወያዩ ማመቻቸት፤
- የተለያዩ ቃላት በቻርት በማቅረብ አብሮ ሂያጅ የሆኑትን እንዲለዩ ማለማመድ፤
- በሃላፊ ጊዜ የተጻፈ አንድ ሞዴል አንቀጽ ወደክፍል በማምጣት ተማሪዎቹ በምሳሌው መሠረት የራሳቸውን እንዲጽፉ ማድረግ፤
- የቱሪስት መስህብ የሆኑ ቦታዎችን በፎቶና በቪዲዮ ማሳየት፤
- እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎችንም መጠቀም ይችላሉ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር! በዚህ ትምህርት ሥር ለማዳመጥ መነሻ የሚሆኑ የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው፤ የሚሰጧቸውንም ምላሾች እንዳለ ይቀበሏቸው። ተማሪዎቹ የተለያዩ መልሶችን ሊሰጡ ስለሚችሉ ለማረም መሞከር አያስፈልግም። ምላሾቹን ከተቀበሉ በኋላ ወደዋናው ትምህርት ይግቡ። በመጀመሪያ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው። በመጀመሪያው ንባብ ተማሪዎች በጸጥታ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። በመቀጠል በቦርድ ላይ የተሰጡትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እያዳመጡ መሥራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው። ከዚያም ባዳመጡት ምንባብ መሠረት የቀረቡትን መልመጃዎችና ተግባራት በትዕዛዞቻቸው መሠረት ያሠሯቸው። የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በቀጣይ ክፍለጊዜ የሚሠሩ ስለሆነ ከማሠራትዎ በፊት ሀሳቡን ለማስታወስ ምንባቡን በድጋሚ ያንብቡላቸው።

## ወንጪ ሐይቅ

የወንጪን ሐይቅ ከአምቦ በስተደቡብ ወደ ወሊሶ በሚወስደው የጠጠር መንገድ ላይ 27 ኪሎ ሜትር ተጉዘን እናገኛለን። ወደ ሐይቁ ከመድረሳችን በፊት በግራና ቀኝ ካለው የጠጠር መንገድ እረፍት የሚደረግበት ከፍ ያለ ቦታ አለ። ከሐይቁ ሳንደርሰ በአካባቢው የሚገኘው የመሬት አቀማመጥና ውበት እንዲሁም ንፁህ አየር እጅግ ማራኪ ነው። የወንጪ ሐይቅ 560 ሄክታር ሰፋት አለው። ጥልቀቱም ከ9 ሜትር እስከ 67.8 ሜትር ይደርሳል። ሐይቁ በተራራው አምባ ላይ ሲገኝ 3,386 ሜትር ከባህር ጠለል በላይ ይገኛል። የወንጪ ሐይቅ በከፊል በደን ተሸፋኗል። በተራራው ላይም ዝንጀሮዎች፣ ጦጣዎች፣ አጋዘኖች ይገኛሉ።

የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አዳዲስ ቃላትና ሐረጋትን በመለየት በደብተራችሁ ላይ ጻፉና በፍቺያቸውን ላይ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።
2. የወንጪ ሐይቅ ከአምቦ ከተማ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?

ሌላው የቱሪስት መስህብ ደግሞ የተፈጥሮ ፍልውሃው ነው። ይህ ሐይቅ በደቡብ ምሥራቅ በኩል የተለያዩ ፍልውሃዎችን ይዟል። እነዚህ ፍልውሃዎችም ፈዋሾች ናቸው ተብለው ስለሚታመንባቸው ብዙ ሰዎች ይጎበኟቸዋል። በዚህ ሐይቅ ውስጥ ሁለት ደሴቶች አሉ። በአንደኛው ደሴት ቂርቆስ የሚባል ገዳም አለ። ወደ ገዳሙም በጀልባ መሻገር ይቻላል። ቱሪስቶችም ከተራራው ወርደው ወደ ሐይቁ በፈረስ ይጓዛሉ። ይህም አንድ ሰዓት ተኩል ይፈጃል። እረፍት ሲፈልጉ ኮረብታው ላይ መናፈሻ ሰላለ ለስላሳና ውሃ ያገኛሉ።

(ምንጭ፡ Ethiopian sustainable Tourist Alliance 2012)

## መልመጃ አንድ

በመልመጃ አንድ ሥር በሁለት ትዕዛዞች ሥር ጥያቄዎች ቀርበዋል። ስለዚህ ጥያቄዎቹን ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ትዕዛዞች መሠረት እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች መልሶቻቸውን በምሳሌ አስደግፈው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት በቡድን ውይይት ማድረግ የሚያስችላቸው ሀሳቦች ቀርበዋል። ስለዚህ ሀሳቦቹን መሠረት በማድረግ ንግግር እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው።

## ተግባር አንድ

በዚህ ተግባር ሥር ንግግር ለማዳበር የሚረዱ ሁለት ተግባራት ቀርበዋል። አንደኛው ተማሪዎች በአከባቢያቸው ከሚገኙ የቱሪስት መስህቦች ሰዎችን በመጠየቅ ወይም በማንበብ ተዘጋጅተው አጭር ንግግር እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አንድን ሐይቅ የመጎብኘት ዕድል ቢያጋጥማቸው ምን ዓይነት ቅድመዝግጅት እንደሚያስፈልግ ሰዎችን በመጠየቅ ለጓደኞቻቸው በንግግር እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ንግግር እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር "የነጭ ሣር ፓርክ" የሚል ምንባብ ቀርቧል። ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ የቅድመንባብ ጥያቄዎች ተሰጥቷል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸውና እንዲመልሱ

ያነሳሷቸው፤ የሚሰጡትንም መልሶች ይቀበሏቸው። ከዚያም ተማሪዎች ምንባቡ ላይ ተመሥርተው የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው።

### መልመጃ ሁለት

በመልመጃ ሁለት ሥር በሁለት የተለያዩ ትእዛዞች ሥር ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ተማሪዎች ባነበቡት ምንባብ መሠረት ለተጠየቁት ጥያቄዎች በቃል መልስ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት ነው። ስለሆነም የጥያቄዎቹን ትዕዛዞች እየተከተሉ ተማሪዎቹ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፤ ግብረምልስም ይስጧቸው።

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ተግባር ሥር ሀላፊ ጊዜን መለየትና መጠቀም የሚያስችሉ ተግባራት ቀርበዋል። በመሆኑም ለተግባራቱ በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።

### ተግባር ሁለት

በዚህ ተግባር ሥር ሦስት የተለያዩ ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው ከቀረበላቸው አንቀጽ ውስጥ የሀላፊ ጊዜ አመልካች ግሶችን ለይተው እንዲያወጡ የሚጠይቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በቀረበላቸው ምሳሌ መሠረት አንድ አንቀጽ በሃላፊ ጊዜ አመልካች ጽፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ሲጠይቅ ሦስተኛው ተማሪዎቹ ከዚህ በፊት አንብበው ከሚያውቁት ጽሑፍ አንድ በሃላፊ ጊዜ ከቀረበ ምንባብ ውስጥ አንድ አንቀጽ መርጠውና የመረጡት አንቀጽ በሃላፊ ጊዜ አመልካች የተገለጸበትን እንዲያሳዩ የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም የቀረቡላቸውን ተግባራት በተሰጣቸው ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ሥር የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ለመለየት የሚያስችላቸው ማስታወሻ እና መልመጃ ቀርቧል። ስለዚህ በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው።

### መልመጃ ሦስት

በዚህ መልመጃ ሥር ሁለት ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው ለቀረቡት ቃላት ፍካሬያዊና እማሬያዊ ፍቺ እንዲሠጡ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከተሰጣቸው ቃላት በተጨማሪ ሌሎች እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ያላቸውን ቃላት እንዲፈልጉ የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር ድኅረአምድ ቅጥያዎችን በመለየት መጠቀም የሚያስችላቸው መልመጃና ማስታወሻ ቀርበዋል። ስለሆነም የቀረቡትን መልመጃዎች በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ አራት

በዚህ መልመጃ ሥር ሁለት የተለያዩ ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው የድኅረአምድ ቅጥያዎች እንዲለዩ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የድኅረአምድ ቅጥያዎችን በመጠቀም ቃላት እንዲመሠርቱ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ናቸው። ስለሆነም በትዕዛዞቻቸው መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## 3. ግምገማ

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መረዳታቸውን በሚከተሉት ነጥቦች ይገምግሙ።

- ተዘጋጅተው መናገር መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- የቃላትን ፍካሬያዊና እማሬያዊ ፍቺ መለየት መቻላቸውን ይገምግሙ።
- የድኅረአምድ ቅጥያዎችን በቃላት ውስጥ መጠቀም መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ሀላፊ ጊዜን በመጠቀም አንቀጽ መጻፍ መቻላቸውን ያረጋግጡ።

# የተመረጡ የመልመጃ ጥያቄዎች  መልስ

## መልመጃ አንድ

### ሀ. የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

1. የወንጪ ሐይቅ 560 ሄክታር ሰፋት አለው።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

### ለ. ቃላትን በምዕላድ ደረጃ መነጣጠል

1. ፍል-ውሃ-ዎች-ም
2. ደሴት-ኦች
3. በ-ተራራ-ዎች
4. ከ-መድረስ-ኣችን
5. ፈዋሽ-ኦች

### ሐ. የተለያዩ ቃላትን ሊሰጡ ይችላሉ።

## መልመጃ ሁለት

ሀ. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

1. ነጭ ሣር ብሔራዊ ፓርክ ስያሜውን ያገኘው በውስጡ ባለው ነጭ የሣር ዓይነት ነው።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

### ለ. ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት

1. እንቁላል በመጣል ሳይሆን ወልደው ጡት በማጥባት የሚራቡ
2. የተለያዩ እንስሳትና ዕፅዋት የሚኖሩበት

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሦስት

### ሀ. የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

| ቃላት | ፍቺ | |
|---|---|---|
| | እማሬያዊ | ፍካሬያዊ |
| እባብ | ተሳቢ እንስሳ | መሰሪ፣ ተንኮለኛ |
| ንብ | ማር የምታዘጋጅ እንሰሳ | ታታሪ፣ ጠንካራ |
| ቤት | መኖሪያ | ትዳር፣ ኑሮ |
| ተልባ | የቅባት እህል ዓይነት | ሙልጭልጭ፣ የማይጨበጥ፣ ቋሚ ባህርይ የሌለው፣ በወዳጅነት የማይዘልቅ፣ ጊዜ አይቶ የሚከዳ |
| ጉንዳን | መሬት ላይ በቡድን የሚንቀሳቀስ ትንሽዬ እንሰሳ | በጣም ብዙ |

### ለ. የተለያዩ ቃላትን ሊያቀርቡ ይችላሉ።

## መልመጃ አራት

ሀ. ድህረአምድ ቅጥያዎችን መለየት

1. -ኦች
2. -ኡ (-ዉ)
3. -ኣን
4. -ኣት
5. -ኣችን
6. -ኡ
7. -ዋ
8. -ነት
9. -ኧት
10. -ነት

### ለ. የተለያዩ ቃላትን ሊሰጡ ይችላሉ።

# ምዕራፍ ስድስት

## ፀረአደንዛዥ ንጥረነገሮች (18 ክፍለጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- ለንባብ ተግባራት ተገቢ የሆኑ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መርጠው ይተገብራሉ፤
- የፅሑፍን መዋቅር ይለያሉ፤
- ለእንግዳ ቃላት ከአውዱ በመነሳት ፍቺ ይሰጣሉ፤ ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ጅምር አንቀጽ አሟልተው ይጽፋሉ፤
- ስለአንድ ርዕሰ ጉዳይ በሚገልፁበት ጊዜ መሸጋገሪያ (አያያዥ) ቃላትን (ሐረጋትን) ይጠቀማሉ፤
- ተውላጠስሞችን በዓረፍተነገር ውስጥ ይጠቀማሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- ስለሲጋራና አስከፊነቱ ሌሎች ተማሪዎች ሲናገሩ ማዳመጥ፤
- ሲጋራ በሰዎች ሕይወት ላይ ስለሚያስከትለው ጉዳት ሌሎች ተማሪዎች ሲናገሩ ማዳመጥ፤
- መምህሩ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላቸውን ምንባብ ማዳመጥ፤

### 2.2. ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- በቡድን ተወያይተው መናገር
- የሚሰጣቸውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ መናገር

### 2.3. ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

- ለቁልፍ ቃላት የሰጡትን ፍቺ ማንበብ
- “ከጫት መገለል” የሚለውን ምንባብ ማንበብ

### 2.4. ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- ጅምር አንቀጽን አሟልቶ መጻፍ፤

### 2.5. ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መጠቀም

### 2.6. ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው

- ተውላጠስሞችን መጠቀም፤
- አያያዥ ቃላት መጠቀም፤

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎችንና ብልሃቶችን መጠቀም፤
- ከዝርዝር ወደአጠቃላይ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የማስተማሪያ ስልቶችን መጠቀም፤
- ተማሪዎችን በቡድን በማከፋፈል እንዲወያዩ ማመቻቸት፤
- የተለያዩ ቃላትን በማቅረብ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺያቸውን እንዲለዩ ማለማመድ፤
- ሞዴል ጅምር አንቀጽ ወደክፍል በማምጣት ተማሪዎችን በማለማመድ የራሳቸውን አሟልተው እንዲጽፉ ማድረግ፤
- እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎችንም መጠቀም ይችላሉ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር! በዚህ ትምህርት ሥር ለማዳመጥ መነሻ የሚሆኑ የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው፤ የሚሰጧቸውንም ምላሾች እንዳለ ይቀበሏቸው። ተማሪዎቹ የተለያዩ መልሶችን ሊሰጡ ስለሚችሉ ለማረም መሞከር አያስፈልግም። ምላሾቹን ከተቀበሉ በኋላ ወደዋናው ትምህርት ይግቡ። በመጀመሪያ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው። በመጀመሪያው ንባብ ተማሪዎች በጸጥታ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። በመቀጠል በቦርድ ላይ የተሰጡትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እያዳመጡ መሥራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው። ከዚያም ባዳመጡት ምንባብ መሠረት የቀረቡትን መልመጃ ጥያቄዎች በትዕዛዞቻቸው መሠረት ያሠሯቸው። የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በቀጣይ ክፍለጊዜ የሚሠሩ ስለሆነ ከማሠራትዎ በፊት ሀሳቡን ለማስታወስ ምንባቡን በድጋሚ ያንብቡላቸው።

## ከሲጋራ የመገለል ጠቀሜታ

ከሱስ አስያዥ ነገሮች አንዱ ሲጋራ ነው። ሲጋራ ሱስ ከማስያዙም በላይ ለጤና ጠንቅ የሆኑ ኬሚካሎች ይገኙበታል። የሚያጨሱ ሰዎች የሲጋራውን ጭስ ወደሳንባቸው በሚስቡበት ጊዜ ኬሚካሎቹ ወደሰውነታቸው ይሠራጫሉ። በዚህ ምክንያት ለሳንባ ካንሰርና ለተለያዩ በሽታዎች ይጋለጣሉ። ሲጋራ የሚያጨሱ ሰዎች ከማያጨሱት ሰዎች ጋር ሲነጻፀሩ በሳንባ ካንሰር የመጠቃት ዕድላቸው ከፍተኛ እንደሆነ ይነገራል። የሲጋራ ሱስ ከጤና ችግር በተጨማሪ ለምጣኔ ሀብታዊ ችግር ያጋልጣል። ሲጋራ የሚያጨሱ ሰዎች ጠረናቸው ከማያጨሱት የተለየ ነው። ይህ ደግሞ ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ያሻክራል።

**የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. አዳዲስ ቃላትን በመለየት በደብተራችሁ ላይ ጻፉና በፍቺያቸው ላይ በጥንድ ተወያይታችሁ ለቃላቱ ፍቺ ስጡ።
2. ሲጋራ ለጤና ጠንቅ የሚሆነው እንዴት ነው?

ስለዚህ ራሳቸውን ከሲጋራ ሱስ ነጻ ያደረጉ ሰዎች በጤንነታቸው፣ በምጣኔ ሀብታቸውና በማህበራዊ ግንኙነታቸው ላይ ችግር አይኖርባቸውም። ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን በተገቢው መምራት ይችላሉ። ሥራቸውን በተገቢው ጊዜና በጥራት ማከናወን ይችላሉ። በሱስ ምክንያት ለሚመጡ የጤና ችግሮችም አይጋለጡም። ገንዘባቸውን ለፈለጉትና ላቀዱት ነገር ማዋል ይችላሉ። ጠንካራ ማህበራዊ ግንኙነት ይኖራቸዋል። በሰዎች ዘንድም ያላቸው ተቀባይነት ይጨምራል። የሚወደዱና የሚከበሩ ጠቃሚ ሰዎች ይሆናሉ። በአጠቃላይ የሲጋራ ሱስ በጤና፣ በምጣኔ ሀብትና በማህበራዊ ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል። ስለዚህ ከሲጋራ ሱስ በመገለል ሕይወትን በአግባቡ መምራት ያስፈልጋል።

## መልመጃ አንድ

በመልመጃ አንድ ሥር የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ስለዚህ ጥያቄዎቹን ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ትዕዛዞች መሠረት እንዲመልሱ ያበረታቷቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች መልሶቻቸውን በምሳሌ አስደግፈው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት በቡድን ውይይት ማድረግ የሚያስችላቸው ሀሳቦች ቀርበዋል። ስለዚህ ሀሳቦቹን መሠረት በማድረግ ንግግር እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው።

## ተግባር አንድ

በዚህ ተግባር ሥር ንግግር ለማዳበር የሚረዱ ሁለት ተግባራት ቀርበዋል። አንደኛው ተማሪዎች በአከባቢያቸው በሲጋራ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች ስለሚያጋጥማቸው ችግሮች በቡድን ተወያይተው የደረሱበትን በተወካዮቻቸው በኩል ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከሲጋራ ሱስ መገለል ያለውን ጠቀሜታ ሰዎችን በመጠየቅ ወይም በማንበብ ባገኙት መረጃ ላይ በቡድን ተወያይተው የደረሱበትን በተወካዮቻቸው በኩል ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ንግግር እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር "ከጫት መገለል" የሚል ምንባብ ቀርቧል። ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ የቅድመንባብ ጥያቄዎች ተሰጥቷል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸውና እንዲመልሱ ያነሳሷቸው፤ የሚሰጡትንም መልሶች ይቀበሏቸው። ከዚያም ተማሪዎች ምንባቡ ላይ ተመሥርተው የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሁለት

በመልመጃ ሁለት ሥር በሦስት የተለያዩ ትእዛዞች ሥር ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ተማሪዎች ባነበቡት ምንባብ መሠረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ እንዲሰጡ የሚጠይቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ከሰጡ በኋላ በቃላቱ ዓረፍተነገር እንዲመሠርቱ የሚጠይቅ ነው። ሦስተኛው ደግሞ በምንባቡ መሠረት የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሑፍ እንዲመልስ የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም የጥያቄዎቹን ትዕዛዞች እየተከተሉ ተማሪዎቹ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፤ ግብረምልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ተግባር ሥር ጅምር አንቀጽን አሟልተው እንዲጽፉ የሚያስችላቸው ተግባራት ቀርበዋል። በመሆኑም ለተግባራቱ በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።

## ተግባር ሁለት

በዚህ ተግባር ሥር ሁለት ጀምር አንቀጾች ቀርበዋል። በመሆኑም ጅምር አንቀጾቹን ሀሳቦችን በማከል አሟልተው እንዲጽፉ ያድርጓቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ሥር የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ለመለየት የሚያስችላቸው መልመጃ ቀርቧል። ስለዚህ በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሦስት

በዚህ መልመጃ ሥር ሦስት ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው ለቀረቡት ቃላት ፍካሬያዊና እማሬያዊ ፍቺ በዓረፍተነገር እንዲጠቀሙ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከተሰጣቸው

ቃላት በተጨማሪ ሌሎች እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ያላቸውን ቃላት እንዲፈልጉ የሚጠይቅ ነው። ሦስተኛው ደግሞ በቀረበላቸው ዓረፍተነገር ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ያላቸው ፍቺ እማሬያዊ ወይም ፍካሬያዊ መሆኑን እንዲለዩ ይጠይቃል። ስለሆነም በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር ተውላጠስሞችንና አያያዥ ቃላት መጠቀም የሚያስችላቸው መልመጃና ማስታወሻ ቀርበዋል። ስለሆነም የቀረቡትን መልመጃዎች በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ አራት

በዚህ መልመጃ ሥር የተሰጡ ተውላጠስሞችን በመጠቀም ዓረፍተነገር እንዲመሠርቱ የሚጠይቅ ጥያቄ ቀርቧል። ስለሆነም በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## ግምገማ

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መረዳታቸውን በሚከተሉት ነጥቦች ይገምግሙ።

- የተለያዩ ጽሑፎችን አዳምጠው መረዳት መቻላቸውን ይገምግሙ።
- ተዘጋጅተው መናገር መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ፅሑፍን አንብበው ያገኙትን መልዕክት ከእውናዊ ህይወታቸው ጋር ማዛመድ መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ጅምር አንቀጾችን ተገቢ ሀሳቦች በማከል አሟልተው መጻፍ መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- የቃላትን ፍካሬያዊና እማሬያዊ ፍቺ መለየት መቻላቸውን ይገምግሙ።
- ተውላጠስሞችንና አያያዥ ቃላት በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም መቻላቸውን ያረጋግጡ።

# የተመረጡ የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ

## መልመጃ አንድ

### ሀ. የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎች

1. አንድ ሰው ሲጋራን በማጨሱ ምክንያት ለሳንባ ካንሰርና ለተለያዩ በሽታዎች ሊጋለጥ ይችላል።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሁለት

**ሀ. እውነት/ሀሰት**

1. እውነት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. እውነት

**ለ. አውዳዊ ፍቺ በመስጠት ዓረፍተነገር መመሥረት**

(የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)

**ሐ. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች**

1. ጫት መቃም ወደድብርት፣ መረበሽና ዕብደት ሊያስገባ ይችላል። የሆድና የአንጀት ድርቀት ያስከትላል። የምግብ ፍላጎት ይቀንሳል። በተሃዋሲያን ምክንያት የሚተላለፉ በሽታዎችን የመከላከል አቅምን ያሳጣል። ለቲቢና ሄፒታይትስ ለመሳሰሉት በሽታዎች ያጋልጣል።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሦስት

**ሀ. የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ**

(የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)

**ለ. (የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)**

**ሐ. የተሰመሬባቸው ቃላት**

1. እማሬያዊ
2. ፍካሬያዊ
3. እማሬያዊ
4. ፍካሬያዊ
5. ፍካሬያዊ
6. ፍካሬያዊ
7. እማሬያዊ
8. እማሬያዊ
9. ፍካሬያዊ
10. እማሬያዊ

## መልመጃ አራት

(የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)

# መልመጃ አምስት

**ሀ. ባዶ ቦታ መሙላት**

1. ነገር ግን
2. ይሁን እንጂ
3. ምክንያቱም
4. ስለዚህ
5. አለበለዚያ
6. ቢሆንም

**ለ. ዓረፍተነገር መመሥረት**

(የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)

**ሐ. ከተሰጡት አማራጮች በመምረጥ ባዶ ቦታ መሙላት**

1. እኛ
2. እሷ
3. እሷ
4. እነሱ
5. አንቺ

# ምዕራፍ ሰባት

## የጥላቻ ንግግር (18 ክፍለጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- አስተያየቶችን አዳምጠው መስማማትና አለመስማማታቸውን ይገልጻሉ፤
- ችግር ለመፍታት የሚያስችላቸውን ሁነት/ጥያቄ ያካተተ የጥላቻ ንግግርን የሚገልፅ ፅሑፍ ያነባሉ፤
- ቅፅሎችን ለይተው ይጠቀማሉ፤
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- አንብበው ተመሳሳይ አስረጅ ጽሑፍ ይጽፋሉ፤
- “እና” እና “ግን”ን በመጠቀም ድርብ ዓረፍተነገሮችን ይጽፋሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- ስለማህበራዊ መገናኛ ጠቀሜታና ጉዳት ሌሎች ተማሪዎች ሲናገሩ ማዳመጥ፤
- መምህሩ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላቸውን ምንባብ ማዳመጥ፤

### 2.2. ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- ስለማህበራዊ መገናኛ ጠቀሜታና ጉዳት የሚያውቁትን መናገር
- ካዳመጡት ምንባብ የተረዱትን መልዕክት መናገር
- የጥላቻ ንግግር በሀገርና በማኅበረሰቡ ላይ ስለሚያስከትለውን ጉዳት መናገር

### 2.3. ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

- የጥላቻ ንግግርን መከላከል ስላለው ጠቀሜታ ማንበብ
- “የጥላቻ ንግግር መከላከያ መንገዶች” የሚለውን ምንባብ ማንበብ

### 2.4. ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- አስረጂ ጽሑፍ መጻፍ፤

### 2.5. ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት

### 2.6. ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው

- አያያዥ ቃላትን መጠቀም፤
- ቅጽሎችን መለየት፤

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎችንና ብልሃቶችን መጠቀም፤
- ከዝርዝር ወደአጠቃላይ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የማስተማሪያ ስልቶችን መጠቀም፤
- ተማሪዎችን በቡድን በማከፋፈል እንዲወያዩ ማመቻቸት፤
- የተለያዩ አያያዥ ቃላት በቻርት በማቅረብ በዓረፍተነገር እንዲጠቀሙ ማለማመድ፤
- ሞዴል አስረጂ ጽሑፍ ወደክፍል በማምጣት ተማሪዎች በምሳሌው መሠረት እንዲጽፉ ማድረግ፤
- እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎችንም መጠቀም ይችላሉ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር! በዚህ ትምህርት ሥር ለማዳመጥ መነሻ የሚሆኑ የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው፤ የሚሰጧቸውንም ምላሾች እንዳለ ይቀበሏቸው። ተማሪዎቹ የተለያዩ መልሶችን ሊሰጡ ስለሚችሉ ለማረም መሞከር አያስፈልግም። ምላሾቹን ከተቀበሉ በኋላ ወደዋናው ትምህርት ይግቡ። በመጀመሪያ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው። በመጀመሪያው ንባብ ተማሪዎች በጸጥታ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። በመቀጠል በቦርድ ላይ የተሰጡትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እያዳመጡ መሥራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው። ከዚያም ባዳመጡት ምንባብ መሠረት የቀረቡትን መልመጃዎችና ተግባራት በትዕዛዞቻቸው መሠረት ያሠሯቸው። የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በቀጣይ ክፍለጊዜ የሚሠሩ ስለሆነ ከማሠራትዎ በፊት ሀሳቡን ለማስታወስ ምንባቡን በድጋሚ ያንብቡላቸው።

## የጥላቻ ንግግርና ማህበራዊ መገናኛዎች

የጥላቻ ንግግር ሁሉን አቀፍ ትርጓሜ ወይም ብያኔ አልተሰጠውም። ብያኔ ሲሰጠውም እንደየአገራቱ ሁኔታ እና አውድ ይወሰናል። ለምሳሌ በተባበሩት መንግስታት እንደተገለጸው የጥላቻ ንግግር በየትኛውም አይነት በንግግር፣ በፅሁፍ ወይም በባህሪ በሚደረግ ግንኙነት (ተግባቦት) ውስጥ፣ አንድን ሰው ወይም ቡድንን በማንነቱ ላይ በመመርኮዝ አግላይ ቋንቋን ተጠቅሞ ማጥቃት ነው። በሌላ አነጋገር አንድን ሰው ወይም ቡድኖችን ሃይማኖታቸውን፣ ብሔራቸውን፣ ጎሳቸውን፣ ዜግነታቸውን፣ ዘራቸውን፣ ቀለማቸውን፣ ፆታቸውን፣ ዕድሜያቸውን ወይም ሌሎች የማንነት መገለጫዎቻቸውን መሠረት በማድረግ የሚሰነዘር ጥቃት ነው። ጥቃቱንም የሚሰነዝሩት የሚያንቋሽሹ ወይም ዝቅ የሚያደርጉና የሚያገልሉ ቃላትን ወይም አባባሎችን በመጠቀም ነው። የጥላቻ ንግግር በግለሰቦችና በቡድኖች የሚሰራጩ ሊሆኑ ይችላሉ። በብዛት የሚሰራጩትም በማህበራዊ ሚዲያዎች አማካኝነት ነው።

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የጥላቻ ንግግር ማለት ምን ማለት ነው?
2. የጥላቻ ንግግር በምን በምን ይገለጻል?

ማህበራዊ መገናኛ ማለት ሰዎች በበይነመረብ አማካኝነት በመገናኘት መረጃዎችን የሚለዋወጡበት ነው። በአሁኑ ወቅት በማህበራዊ መገናኛ ዘርፍ አለም አቀፍ ታዋቂነት ያላቸው እንደነፌስቡክ፣ ትዊተር፣ እንስታግራም፣ ቴሌግራም፣ ዩቱብ፣ ወዘተ. በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። ማህበራዊ መገናኛዎቹ መረጃን በፍጥነት ከማድረስ ረገድ ጠቃሚነታቸው የጎላ ነው። ይሁን እንጂ በመገናኛዎቹ የሚሠራጩ መረጃዎች በጥንቃቄ ካልተመረጡ በማህበረሰቡ ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም በማህበራዊ ሚዲያዎች አማካኝነት ግለሰቦች የራሳቸውን አመለካከት፣ ሀሰተኛ መረጃዎችና ማንነትን መሠረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮችን በስፋት ሊያሰራጩባቸው ይችላሉ። ለምሳሌ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን ከፍተኛ የሆኑ የሀሰተኛ መረጃዎችና የጥላቻ ንግግሮች ተስፋፍተዋል። በዚህም ምክንያት ሀገራዊ አንድነትን ከመሸርሸር አልፎ በሰዎች ሕይወትና ንብረት ላይ ጉዳቶች ደርሰዋል። ስለሆነም መንግሥት የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጀዎችን ስርጭት ለመከላከል ህጎችን አውጥቶ እየሠራ ይገኛል። ስለዚህ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን ጥንቃቄ የተሞላበት ሊሆን ይገባል።

### መልመጃ አንድ

በመልመጃ አንድ፤ ሁለት ትዕዛዞች ሥር የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል። አንደኛው ባዳመጡት መሠረት በቃል መልስ የሚሰጡበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በቀረበላቸው ሀሳቦች ላይ በቡድን በመወያየት የደረሱበትን በተወካዮቻቸው በኩል ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ነው። ስለዚህ ጥያቄዎቹን ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ትዕዛዞች መሠረት እንዲመልሱ ወይም እንዲሠሩ ያበረታቷቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች መልሶቻቸውን በምሳሌ አስደግፈው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ንግግር ለማድረግ የሚያስችላቸው ሀሳቦች ቀርበዋል። ስለዚህ ሀሳቦቹን መሠረት በማድረግ ንግግር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።

### ተግባር አንድ

በዚህ ተግባር ሥር ንግግር ለማድረግ የሚረዱ ሁለት ተግባራት ቀርበዋል። አንደኛው ተማሪዎች ካዳመጡት ምንባብ የተረዱትን መልዕክት በንግግር እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የጥላቻ ንግግር በሀገርና በማኅበረሰብ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ሰዎችን በመጠየቅ

ወይም በማንበብ ያገኙትን መረጃ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ንግግር እንዲያደርጉ ያድርጉ።

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር "የጥላቻ ንግግር መከላከያ መንገዶች" የሚል ምንባብ ቀርቧል። ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ የቅድመንባብ ጥያቄዎች ተሰጥቷል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸውና እንዲመልሱ ያነሳሷቸው፤ የሚሰጡትንም መልሶች ይቀበሏቸው። ከዚያም ተማሪዎች ምንባቡ ላይ ተመሥርተው የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው።

### መልመጃ ሁለት

በመልመጃ ሁለት ሥር በሁለት የተለያዩ ትእዛዞች ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ተማሪዎች ባነበቡት ምንባብ መሠረት ጥያቄዎችን በቃል መልስ የሚሰጡበት ነው። በመሆኑም ለጥያቄዎቹ በቃል መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ የተሳሳቱ ምላሾች ከሰጡ ትክክለኛ የሆኑትን መልሶች በመንገር ተማሪዎቹን ይርዷቸው። ሁለተኛው ደግሞ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሠጡ የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም ከምንባቡ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ መልሶቻቸውንም በማስተካከል ያግዟቸው።

### መልመጃ ሦስት

በዚህ መልመጃ ሥር በ "ሀ" ሥር የቀረቡት የምንባቡ ዋናዋና ሀሳቦች በየትኛው የምንባቡ አንቀጽ እንደተገለጹ ከ "ለ" ስር በመምረጥ በማዛመድ የሚመለሱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ስለዚህ ተማሪዎቹ በምንባቡ መሠረት እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ተግባር ሥር አስረጂ ጽሁፍ ለመረዳትና ለመጻፍ የሚያስችላቸው ማስታወሻና ተግባራት ቀርበዋል። በመሆኑም ለተግባራቱ በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።

### ተግባር ሁለት

በዚህ ተግባር ሥር አስረጂ ጽሁፍ ለመጻፍ የሚያስችሏቸው ሁለት ሀሳቦች ቀርበዋል። በመሆኑም በተሰጣቸው ሀሳቦች መነሻነት አስረጂ ጽሑፍ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ሥር ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ለመስጠት የሚያስችላቸው መልመጃ ቀርቧል። ስለዚህ በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ አራት

በዚህ መልመጃ ሥር ሁለት ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው በተሰጣቸው ቃላት ዓረፍተነገር በመሥራት አውዳዊ ፍቺአቸውን በመስጠት የሚመለሱ ናቸው። ሁለተኛው ደግሞ በዓረፍተነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ በመስጠጥ መልስ የሚሰጡበት ነው። ስለሆነም በትዕዛዙ መሠረት እንዲሠሩ ያድርጉ፤ ለመልሶቻቸውም ማስተካከያ ይስጧቸው።

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር አያያዥ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገር ለመጻፍ የሚያስችላቸው መልመጃ ቀርቧል። በተጨማሪም ቅጽሎችን ለመለየት የሚያስችላቸው መልመጃና ማስታወሻ ቀርበዋል። ስለሆነም የቀረቡትን መልመጃዎች በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት እንዲሠሩ ያድርጉ።

## መልመጃ አምስት

በዚህ መልመጃ ሥር ሁለት የተለያዩ ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው "እና" እና "ግን"ን በመጠቀም ተማሪዎች አምስት ድርብ ዓረፍተነገሮች በመመሥረት የሚመልሷቸው ናቸው። ሁለተኛው ደግሞ የቀረቡላቸውን ድርብ ዓረፍተነገሮች በመነጣጠል የተለያዩ ነጠላ ዓረፍተነገሮችን እንዲጽፉ የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም ተማሪዎቹ ድርብ ዓረፍተነገር እንዲመሠርቱና ከድርብ ዓረፍተነገሮች ነጠላ ዓረፍተነገሮችን ለይተው እንዲያሳዩ ያድርጉ፤ ማስተካከያ በመስጠትም ይርዷቸው።

### 3. ግምገማ

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መረዳታቸውን በሚከተሉት ነጥቦች ይገምግሙ።

- ስለማህበራዊ መገናኛ ጠቀሜታና ጉዳት መናገር መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ያዳመጡትን ምንባብ መልዕክቱን መረዳታቸውን ያረጋግጡ።
- የጥላቻ ንግግር በሀገርና በማኅበረሰቡ ላይ ስለሚያስከትለው ጉዳት መናገራቸውን ያረጋግጡ።
- የተሰጣቸውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ አንቀጽ መጻፍ መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- አስረጂ ጽሑፍ መጻፍ መቻላቸውን ይገምግሙ።
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን ይገምግሙ።
- ቅጽሎችን መለየት መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- አያያዥ ቃላትን በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም መቻላቸውን ይከታተሉ።
- ድርብ ዓረፍተነገሮችን መመሥረት መቻላቸውን ይከታተሉ።
- ቅጽሎችን መለየትና በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ተውላጠስሞችን በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም መቻላቸውን ይገምግሙ።
- ድርብ ዓረፍተነገሮችን ወደ ነጠላ ዓረፍተነገር መከፋፈል መቻላቸውን ያረጋግጡ።

# የተመረጡ የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ

## መልመጃ አንድ

**ሀ. የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

1. የጥላቻ ንግግር አንድን ሰው ወይም ቡድኖችን ሃይማኖታቸውን፣ ብሔራቸውን፣ ጎሳቸውን፣ ዜግነታቸውን፣ ዘራቸውን፣ ቀለማቸውን፣ ፆታቸውን፣ ዕድሜያቸውን ወይም ሌሎች የማንነት መገለጫዎቻቸውን መሰረት በማድረግ የሚሰነዘር ጥቃት ነው።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

**ለ. ተማሪዎቹን በቡድን ያደራጇቸው፤ ሀሳቦቻቸውን እንዲለዋወጡ ጊዜ ይስጧቸው። ከተወያዩ በኋላ በተወካዮቻቸው መሠረት እንዲያቀርቡ ያድርጉ።**

## መልመጃ ሁለት

**ሀ. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች**

1. የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል የሚረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐግብሮችን የማዘጋጀት ኋላፊነት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ነው።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

**ለ. ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት**

1. እገዳ ወይም ተቀባይነት የሌለው
2. ምደባ

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሦስት

# አዛምድ

1. ለ
2. መ
3. ሐ
4. ለ

## መልመጃ አራት

ሀ. (የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)

ለ. አገባባዊ ፍቺ መስጠት

1. መለየት
2. መመርመር
3. እንዳይፈስ ማገድ
4. መከላከል
5. ተጠቀመ
6. አቆየ

## መልመጃ አምስት

ሀ. ድርብ ዓረፍተነገሮችን መመስረት (የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)

ለ. ድርብ ዓረፍተነገሮችን መነጠል

1. አስቴር ትምህርት ቤት ሄዳለች። አስቴር ክፍል ውስጥ አልነበረችም።
2. ቶሎሳ ተፈጥሮን ማድነቅ ይወዳል። ቶሎሳ ልቦለድ ጽሑፎችን አያነብም።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ስድስት

ሀ. ቅጽሎችን መለየት

1. ነጭ
2. ወፍራም

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

ለ. ዓረፍተነገሮችን መመስረት (የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)

# ምዕራፍ ስምንት

# ኤችአይቪ/ኤድስ (18 ክፍለጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- የተማሩትን ውስብስብ የቀለም መዋቅር የተላበሱ ቃላት ቀስ በቀስ እያደገ በሚሄድ አፈፃፀም ፊደላቱን ጠብቀው ይጽፋሉ፤
- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን አስረጅ ፅሑፍ ያነባሉ፤ ቀጥሎ የራሳቸውን ሀሳብ ይፅፋሉ፤
- የድርሰት አላባዊያንን ይለያሉ፤
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ሳቢ እና ኢ-ሳቢ ግሶችን ይለያሉ፤
- ስነምዕላዳዊ ፍቺን ይለያሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- “ኤችአይቪ እና ኤድስ” በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ ሲነበብ ማዳመጥ፤
- ሌሎች ተማሪዎች ከሚነበብላቸው ምንባብ የተረዱትን ማዳመጥ፤

### 2.2. ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- ካዳመጡት ምንባብ የተረዱትን መልዕክት መናገር
- በሚሰጣቸው ርዕሰጉዳይ ላይ ክርክር ማድረግ
- ስለኤችአይቪ/ኤድስ የሚያውቁትን መናገር

### 2.3. ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

- “ኤድስና መንስዔዎቹ” የሚለውን ምንባብ ማንበብ
- የሚመሠርቷቸውን ዓረፍተነገሮች ማንበብ

### 2.4. ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- አስረጂ ጽሑፍ መጻፍ፤

### 2.5. ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት፤

### 2.6. ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

- ሳቢ እና ኢ-ሳቢ ግሶችን መለየት፤
- ስነምዕላዳዊ ፍቺ መስጠት፤

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎችንና ብልሃቶችን መጠቀም፤
- ከዝርዝር ወደአጠቃላይ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የማስተማሪያ ስልቶችን መጠቀም፤
- ተማሪዎችን በቡድን በማከፋፈል እንዲወያዩ ማመቻቸት፤
- የተለያዩ ቃላት በቻርት በማቅረብ ተቃራኒዎቻቸውን እንዲለዩ ማለማመድ፤
- ሞዴል አስረጂ ጽሑፍ በማምጣት ተማሪዎች በምሳሌው መሠረት እንዲጽፉ ማድረግ፤
- እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎችንም መጠቀም ይችላሉ።

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር! በዚህ ትምህርት ሥር ለማዳመጥ መነሻ የሚሆኑ የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው፤ የሚሰጧቸውንም ምላሾች እንዳለ ይቀበሏቸው። ተማሪዎቹ የተለያዩ መልሶችን ሊሰጡ ስለሚችሉ ለማረም መሞከር አያስፈልግም። ምላሾቹን ከተቀበሉ በኋላ ወደዋናው ትምህርት ይግቡ። በመጀመሪያ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው። በመጀመሪያው ንባብ ተማሪዎች በጸጥታ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። በመቀጠል በቦርድ ላይ የተሰጡትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እያዳመጡ መሥራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው። ከዚያም ባዳመጡት ምንባብ መሠረት የቀረቡትን መልመጃዎችና ተግባራት በትዕዛዞቻቸው መሠረት ያሠሯቸው። የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በቀጣይ ክፍለጊዜ የሚሠሩ ስለሆነ ከማሠራትዎ በፊት ሀሳቡን ለማስታወስ ምንባቡን በድጋሚ ያንብቡላቸው።

# ኤችአይቪ እና ኤድስ

ኤችአይቪ እና ኤድስ ብዙ ጊዜ አንድ (ተመሳሳይ) ፍቺ ያላቸው ተደርገው ሲወሰዱ ቆይቷል። ነገር ግን ኤችአይቪ እና ኤድስ የተለያየ ትርጉም አላቸው። ኤችአይቪ የምህጻረ ቃሉ ትንታኔ የሚል ነው። ትርጉሙም የሰውን በሽታ ተከላካይ ሴልን የሚያጠቃ በሽታ ማለት ነው። ኤችአይቪ በደም ውስጥ ገብቶ መሰራጭት ሲጀምር ያ ሰው በበሽታው ተያዘ ማለት ነው። መከላከያ ካልወሰዱበት የበሽታ ተከላካይ የሰውነት ክፍልን በመጉዳት ወደፊት ምንም ዓይነት በሽታ መከላከል እንዳይቻል ያደርጋል። ስለዚህም ተጠቂው ከባድ በሽታ ላይ ይወድቃል፣ ሊሞትም ይችላል። እንግዲህ ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ኤድስ በመባል ይታወቃል።

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ካዳመጣችሁት ምን እንደተረዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. ኤችአይቪ እና በኤድስ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

አንድ ሰው ኤችአይቪ አለበት ማለት ግን ይሞታል ማለት አይደለም። ያለ መከላከያ እንኳን ለብዙ ዘመናት ሊኖር ይችላል። በተጨማሪም በሽታው መከላከያ መድኃኒት አለው። መድኃኒቱ

ደግሞ በሽታው በሽታ ተከላካይ የሰውነት ክፍልን ጎድቶ ወደ ኤድስ እንዳይቀየር ኃይሉን ያዳክማል። በዚህም ብዙ ሰዎች ኤችአይቪ እያለባቸው በጤንነት ኑሮአቸውን እየመሩ ይገኛሉ።

## መልመጃ አንድ

በመልመጃ አንድ፣ ሁለት ትዕዛዞች ሥር የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል። አንደኛው ባዳመጡት መሠረት በቃል መልስ የሚሰጡበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እውነት ወይም ሀሰት በማለት የሚመልሷቸው ናቸው። ስለዚህ ጥያቄዎቹን ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ትዕዛዞች መሠረት እንዲመልሱ ወይም እንዲሠሩ ያበረታቷቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተማሪዎች መልሶቻቸውን በምሳሌ አስደግፌው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፣ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ክርክር ለማካሄድ የሚያስችላቸው ማስታወሻና ተግባራት ቀርበዋል። ስለዚህ ሀሳቦቹን መሠረት በማድረግ ክርክር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።

## ተግባር አንድ

በዚህ ተግባር ሥር ንግግር ለማድረግ የሚረዱ ሁለት ተግባራት ቀርበዋል። አንደኛው ተማሪዎች በኤችአይቪ/ኤድስ የተጠቃን ሰው ማግለል ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ሀሳብ በመደገፍ ወይም በመቃወም በቡድን እንዲከራከሩ የሚደርግ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የኤችአይቪ/ኤድስ ሥርጭትን በመቀነስ ረገድ ከጤና ተቋማት እና ከትምህርት ቤት የበለጠ አስተዋጽዖ ማድረግ ያለበት ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ ሰዎችን በመጠየቅ አሳማኝ መረጃ እያቀረቡ የሚከራከሩበት ነው። ስለሆነም በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ክርክር እንዲያካሂዱ ያድርጉ። ክርክራቸውን ሲያደርጉ የተሰጣቸውን ማስታወሻ እንዲጠቀሙ ያበረታቷቸው።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር "ኤድስና መንስዔዎቹ" የሚል ምንባብ ቀርቧል። ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ የቅድመንባብ ጥያቄዎች ተሰጥቷል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸውና እንዲመልሱ ያነሳሷቸው፣ የሚሰጡትንም መልሶች ይቀበሏቸው። ከዚያም ተማሪዎች ምንባቡ ላይ ተመሥርተው የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሁለት

በመልመጃ ሁለት ሥር በሁለት የተለያዩ ትእዛዞች ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ተማሪዎች ባነበቡት ምንባብ መሠረት ጥያቄዎችን በቃል መልስ የሚሰጡበት ነው። በመሆኑም ለጥያቄዎቹ በቃል መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፣ የተሳሳቱ ምላሾች ከሰጡ ትክክለኛ የሆኑትን መልሶች በመንገር ተማሪዎቹን ይርዷቸው። ሁለተኛው ደግሞ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሠጡና በቃላቱ ዓረፍተነገር እንዲመሰርቱ የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም ከምንባቡ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፣ መልሶቻቸውንም በማስተካከል ያግዟቸው።

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ተግባር ሥር አስረጅ ጽሑፍን እንዲጽፉ የሚያስችላቸው ተግባራት ቀርበዋል። በመሆኑም ለተግባራቱ በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ያሠሯቸው።

### ተግባር ሁለት

በዚህ ተግባር ሥር አስረጅ ጽሑፍን ለመጻፍ የሚያስችሏቸው ሁለት ተግባሮች ቀርበዋል። በመሆኑም በተሰጣቸው ትዕዛዞች መሠረት በአንቀጽ ደረጃ እንዲጽፉ ያድርጓቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ሥር ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ለመስጠት የሚያስችላቸው መልመጃ ቀርቧል። ስለዚህ በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው።

### መልመጃ ሦስት

በዚህ መልመጃ ሥር ሁለት ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው ለተሰጣቸው ቃላት ተቃራኒ ፍቺያቸውን በመስጠት የሚመልሷቸው ሲሆኑ ሁለተኛው በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ መልስ የሚሰጡባቸው ናቸው። ስለሆነም በትዕዛዙ መሠረት እንዲሠሩ ያድርጉ፤ ለመልሶቻቸውም ማስተካከያ ይስጧቸው።

## ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር ስለሳቢ እና ኢ-ሳቢ ግሶች ልዩነት እንዲሁም ስነምዕላዳዊ ፍቺ መስጠትን እንዲማሩ የሚያስችላቸው ማስታወሻና መልመጃ ቀርቧል። በተጨማሪም ቅጽሎችን ለመለየት የሚያስችላቸው መልመጃና ማስታወሻ ቀርበዋል። ስለሆነም የቀረቡትን መልመጃዎች በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት እንዲሠሩ ያድርጉ።

### መልመጃ አራት

በዚህ መልመጃ ሥር ተማሪዎች በተሰጡት ቃላት ላይ ያሉ የድኅረአምድ ቅጥያ ምዕላዶች ያላቸውን ፍቺ በጽሑፍ እንዲሰጡ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ስለዚህ ተማሪዎቹ ለድኅረአምድ ቅጥያ ምዕላዶቹ በጽሑፍ ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፤ ማስተካከያ በመስጠትም ይርዷቸው።

### ግምገማ

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መረዳታቸውን በሚከተሉት ነጥቦች ይገምግሙ።

- በተሰጣቸው ርዕስ ላይ የክርክር መርሆዎችን ጠብቀው ክርክር ማድረግ መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ያዳመጡትን ምንባብ መልዕክቱን መረዳታቸውን ይገምግሙ።
- የድርሰት አላባውያንን መለየት መቻላቸውን ያረጋግጡ።

- አስረጂ ድርሰት መጻፍ መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን ይገምግሙ።
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን ይገምግሙ።
- ስነምዕላዳዊ ፍቺን መለየት መቻላቸውን ይከታተሉ።
- ሳቢ እና ኢ-ሳቢ ግሶችን በመለየት በዓረፍተነገር መጠቀም መቻላቸውን ያረጋግጡ።

## የተመረጡ የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ
## መልመጃ አንድ

### ሀ. የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

1. አንድ ሰው በበሽታው ተያዘ የሚባለው ኤችአይቪ በደም ውስጥ ገብቶ መሰራጭት ሲጀምር ነው።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

### ለ. እውነት/ሀሰት

1. ሀሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሀሰት

## መልመጃ ሁለት

### ሀ. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

1. ስለታም ነገሮችን በጋራ መጠቀም እና ልቅ የግብረሥጋ ግንኙነት መፈጸም ዋነኞቹ ናቸው።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

### ለ. ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠትና በቃላቱ ዓረፍተነገር መመሥረት

(የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)

## መልመጃ ሦስት

### ሀ. የቃላት ተቃራኒ ፍቺ

1. መበርታት
2. መሸፈን፣ ማምለጥ
3. በግል
4. ማስታወስ
5. ግልጽ

**ለ. አዛምድ**

1. ቀ
2. ረ
3. ለ
4. ሸ
5. ሀ
6. ሰ
7. መ
8. ሠ
9. ሐ

## መልመጃ አራት

1. በጎች = በግ-ኦች (ቁጥር አመልካች ወይም ከአንድ በላይ መሆናቸውን)
2. አጠበ = አጠብ-ኧ (መደብ አመልካች)
3. ልብሴ = ልብስ-ኤ (ዘርፍ አመልካች ወይም ባለንብረትነትን)
4. ሰውዬው = ሰውዬ-ው (እምርነት አመልካች)
5. ድስቱ = ድስት-ኡ (እምርነት አመልካች)
6. አበባዎች = አበባ-ዎች (ቁጥር አመልካች ወይም ከአንድ በላይ መሆናቸውን)

## መልመጃ አምስት

1. ለሚ ዛፍ ቆረጠ። (ሳቢ)
2. አልማዝ ገበያ ሄደች። (ሳቢ)
3. ካሳሁን ልብሱን ቀደደ። (ሳቢ)
4. ፋጡማ ፈተና ስላለፈች ተደሰተች። (ኢ.ሳቢ)
5. ለሊሴ መስኮቱን ከፈተች። (ሳቢ)

**ለ. (የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)**

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ልማዳዊ ተግባራት (18 ክፍለጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- የሚነበብላቸውን ታሪክ ያዳምጣሉ፤
- በአስተያየቶች ላይ መስማማት አለመስማማታቸውን ይገልጻሉ፤
- ቀለል ያለና አጭር ታሪክን በማንበብ ዋናውን ሀሳብ ወደ ሰንጠረዥ ያሸጋግራሉ፤
- ካነበቡት ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተያያዘ አጭር አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- የሥራ ማመልከቻ ደብዳቤ ይጽፋሉ፤
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- የሃላፊ ጊዜ ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገር ይመሠርታሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- “የአበራሽ ታሪክ” በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ ሲነበብ ማዳመጥ፤
- ሌሎች ተማሪዎች ከባህላዊ ልማድ ጋር በተያያዘ ስለሚፈጸሙ ተግባራት ሲናገሩ ማዳመጥ፤

### 2.2. ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- በሚሰጣቸው ርዕሰጉዳይ ላይ መናገር፤
- ስለጎጂ ልማዳዊ ተግባራት የሚያውቁትን መናገር፤
- የምንባቡን ዋና መልዕክት መናገር፤

### 2.3. ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

- “ያለዕድሜ ጋብቻ” የሚለውን ምንባብ ማንበብ፤
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በማንበብ መመለስ፤
- ያለዕድሜ ጋብቻን ለመከላከል  ከባለድርሻ አካላት ምን እንደሚጠበቅ ማንበብ፤

### 2.4. ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- የማመልከቻ ደብዳቤ መጻፍ፤
- ካነበቡት ምንባብ ጋር ተያያዥነት ያለው አንቀጽ መጻፍ፤

### 2.5. ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት፤

### 2.6. ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው

- የሃላፊ ጊዜ ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገር መመሥረት፤

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎችንና ብልሃቶችን መጠቀም፤
- ከዝርዝር ወደአጠቃላይ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የማስተማሪያ ስልቶችን መጠቀም፤
- ስለልማዳዊ ተግባራት ጉዳት በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ፤
- ሞዴል የሥራ ማመልከቻ ደብዳቤዎችን በክፍል ውስጥ በማቅረብ ተማሪዎቹ እንዲለማመዱ ማድረግ፤
- በሃላፊ ጊዜ የተጻፉ ሞዴል ዓረፍተነገሮችና አንቀጾችን በክፍል ውስጥ በማቅረብ ተማሪዎቹ እንዲለማመዱ ማድረግ፤
- የተለያዩ ቃላት በቻርት በማቅረብ ተቃራኒዎቻቸውን እንዲለዩ ማለማመድ፤
- እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎችንም መጠቀም ይችላሉ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር! በዚህ ትምህርት ሥር ለማዳመጥ መነሻ የሚሆኑ የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው፤ የሚሰጧቸውንም ምላሾች እንዳለ ይቀበሏቸው። ተማሪዎቹ የተለያዩ መልሶችን ሊሰጡ ስለሚችሉ ለማረም መሞከር አያስፈልግም። ምላሾቹን ከተቀበሉ በኋላ ወደዋናው ትምህርት ይግቡ። በመጀመሪያ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው። በመጀመሪያው ንባብ ተማሪዎች በጸጥታ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። በመቀጠል በቦርድ ላይ የተሰጡትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እያዳመጡ መሥራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው። ከዚያም ባዳመጡት ምንባብ መሠረት የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዞቻቸው መሠረት ያሠሯቸው፤ ግብመልስም ይስጧቸው። የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በቀጣይ ክፍለጊዜ የሚሠሩ ስለሆነ ከማሠራትዎ በፊት ሀሳቡን ለማስታወስ ምንባቡን በድጋሚ ያንብቡላቸው።

## የአበራሽ ታሪክ

አበራሽ በአንዲት የገጠር መንደር የምትኖር ባለትዳር እናት ናት። ዕድሜያቸው ሦስት፣ ሁለት እና አንድ ዓመት የሚሆናቸው ሦስት ልጆች አሏት። የመጀመሪያ ልጅዋን ያረገዘችው እናት ለመሆን በነበራት ጉጉት እና መውለድ እንደምትችል ለማረጋገጥ ፈልጋ ነበር። የመጀመሪያ ልጇን ከወለደች በኋላ ሳታረግዝ ትንሽ መቆየት ብትፈልግም ሁለተኛና ሦስተኛ ልጆቿ ካሰበችው ጊዜ ቀድመው ተወለዱ። ስለቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትም አታውቅም። አበራሽ ልጆቿን በሙሉ የወለደቻቸው በመንደሯ የልምድ አዋላጅ በመታገዝ ነበር። ልጆቿም የከሱ፣ የሰውነት

እድገታቸውም አዝጋሚ የሆነና በተደጋጋሚ በተቅማጥ በሽታ የሚጠቁ ናቸው። አበራሽ አሁን አራተኛ ልጇን አርግዛለች። ስለሆነም ከወትሮው በተለየ መልኩ ድካምና የጤና ማጣት ስሜት ይሰማታል። የቅድመወሊድ ጤና ክትትል ስለማታውቅ በፊት እንደነበሩት እርግዝናዎቿ ሁሉ "ይሄኛውም ከሌሎቹ የተለየ አይደለም" ብላ አሰበች።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አበራሽ የምትኖረው የት ነው?
2. በምታዳምጡበት ጊዜ ዋና ዋና ሀሳቦችን በማስታወሻ መዝግቡ፤ያልተረዳችኋቸው እንግዳ ቃላት ካጋጠሟችሁም ለይታችሁ ጻፉና ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት።

አበራሽ የዘጠኝ ወር እርጉዝ ስትሆን ምጥ ጀመራት። ከሁለት ቀናት ምጥ በኋላ ከባድ የጀርባና የሆድ ህመም ተሰማት። ነገር ግን ልትወልድ አልቻለችም። የልምድ አዋላጇ ልትረዳት ባለመቻሏ ቤተሰቦቿ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛዋን ለእርዳታ ጠሯት። የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛዋም አበራሽን በጣም ደክማና ከማህፀኗ ደም እየፈሰሳት አገኘቻት። ቤተሰቦቿንም በአቅራቢያቸው ወደሚገኘው የጤና ጣቢያ ወዲያው እንዲወስዷት መከረቻቸው። ቤተሰቦቿም አበራሽን "በቃሬዛ ወደ ጤና ጣቢያው መውሰድ አለብን" ብለው ለመወሰን አንድ ተጨማሪ ቀን ፈጀባቸው። ጤና ጣቢያ ደርሰው አዋላጅ ነርሷ ስትመረምራት አበራሽ በጠና መታመሟንና ጽንሱም በሕይወት እንደሌለ አወቀች። አበራሽ ልማዳዊ ተግባራትን በመከተሏ ህይወቷንም ሆነ ልጇን ለአደጋ አጋልጣለች።

(የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተቀናጀ ማጠናከሪያ ሥልጠና ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ሞጁል ሁለት፡ የአሠልጣኞች መመሪያ። 2004። አዲስ አበባ)

## መልመጃ አንድ

በመልመጃ አንድ፤ ሁለት ትዕዛዞች ሥር የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል። አንደኛው ካዳመጡት ምንባብ የወጡ በቃል የሚመለሱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በሁለተኛው ደግሞ እውነት ወይም ሀሰት በማለት ምክንያት እያቀረቡ በጽሑፍ የሚመልሷቸው ናቸው። ስለዚህ ጥያቄዎቹን ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ትዕዛዞች መሠረት እንዲመልሱ ወይም እንዲሠሩ ያበረታቷቸው። የተሳሳተ መልስ ከሰጡ በምንባቡ መሠረት ያስተካክሏቸው።

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት በተሰጣቸው ርዕስ ላይ ንግግር ማድረግ የሚያስችላቸው ተግባራት ቀርበዋል። ስለዚህ ሀሳቦቹን መሠረት በማድረግ ንግግር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።

### ተግባር አንድ

በዚህ ተግባር ሥር ንግግር ለማድረግ መነሻ የሚሆኑ ሦስት ጥያቄዎች ቀርበዋል። አንደኛው በአበራሽ ታሪክ ውስጥ ያሉት ዋና ዋና ክስተቶች ምንምን እንደሆኑ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ የሚጠይቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ክስተቶቹ በምን ምክንያት የተፈጠሩ የራሳቸውን ሀሳብ በንግግር እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ሲሆን ሦስተኛው በአበራሽ ላይ የደረሰው ነገር በሌሎች እናቶች ላይ እንዳይከሰት ከባለታሪኳ፣ ከቤተሰብ፣ ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና ከኅብረተሰቡ፣ ከመንግሥት ምን እንደሚጠበቅ በቡድን ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ንግግር እንዲያደርጉ ያድርጉ።

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር "ያለዕድሜ ጋብቻ" የሚል ምንባብ ቀርቧል። ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ የቅድመንባብ ጥያቄዎች ተሰጥቷል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸውና እንዲመልሱ ያነሳሷቸው፤ የሚሰጡትንም መልሶች ይቀበሏቸው። ምንባቡን ሲያነቡ የምንባቡን ሀሳብ እየተረዱ በየግላቸው ድምፅ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ይንገሯቸው። ከዚያም ተማሪዎች ምንባቡ ላይ ተመሥርተው የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው።

### መልመጃ ሁለት

በመልመጃ ሁለት ሥር በአራት የተለያዩ ትእዛዞች ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ተማሪዎች ባነበቡት ምንባብ መሠረት በቃል መልስ የሚሰጡበት ሲሆን ሁለተኛው ባነበቡት ምንባብ መሠረት ያለዕድሜ ጋብቻ የሚፈጸምባቸውን ዋናዋና ምክንያቶችና የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች በሠንጠረዥ ለይተው እንዲያስቀምጡ የሚጠይቅ ነው። ሦስተኛው ደግሞ ያለዕድሜ ጋብቻን ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ምን እንደሚጠበቅ በሠንጠረዥ እንዲሞሉ የሚጠይቅ ሲሆን አራተኛው ቃላትን በተገቢው ቦታ በማስገባት አውዳዊ ፍቺአቸውን እንዲያሳዩ የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም ተማሪዎቹ ለጥያቄዎቹ ተገቢ መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ የተሳሳቱ ምላሾች ከሰጡ ትክክለኛ የሆኑትን መልሶች በመንገር ተማሪዎቹን ይርዷቸው።

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ተግባር ሥር የማመልከቻ ደብዳቤ እንዲጽፉ የሚያስችላቸው ተግባራት ቀርበዋል። በመሆኑም ለተግባራቱ በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት እንዲሠሩ ያግዟቸው።

### ተግባር ሁለት

በዚህ ተግባር ሥር ሁለት ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው በተሰጣቸው ምሳሌ መሠረት የራሳቸውን የሥራ ማመልከቻ ጥያቄ እንዲጽፉ የሚጠይቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ "ያለዕድሜ ጋብቻ" ከሚለው ምንባብ ጋር ተያያዥነት ያለው የራሳቸውን አንድ አንቀጽ እንዲጽፉ የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ሥር ቃላትን በተቃራኒ ፍቺ ለማዛመድ የሚያስችላቸው መልመጃ ቀርቧል። ስለዚህ በትዕዛዙ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሦስት

በዚህ መልመጃ ሥር በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ"ለ" ረድፍ በመምረጥ መልስ የሚሰጡባቸው ናቸው። ስለሆነም በትዕዛዙ መሠረት እንዲሠሩ ያድርጉ፤ ለመልሶቻቸውም ማስተካከያ ይስጧቸው።

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር የሃላፊ ጊዜ ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገር ለመመሥረት የሚያስችላቸው መልመጃ ቀርቧል። ስለሆነም የቀረቡትን መልመጃዎች በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት እንዲሠሩ ያድርጉ።

## መልመጃ አራት

በዚህ መልመጃ ሥር ሦስት ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው የሃላፊ ጊዜ ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን እንዲመሠርቱ የሚጠይቁ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ከቀረቡት ዓረፍተነገሮች በሃላፊ ጊዜ የቀረቡትን እንዲለዩ የሚጠይቅ ሲሆን ሦስኛው በሃላ ጊዜ ግሶች በመጠቀም አንቀጽ እንዲጽፉ የሚጠይቅ ነው። ስለዚህ ተማሪዎቹ የሃላፊ ጊዜ ግሶችን በጽሑፋቸው ውስጥ እንዲጠቀሙ ያድርጉ፤ ማስተካከያ በመስጠትም ይርዷቸው።

## ግምገማ

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መረዳታቸውን በሚከተሉት ነጥቦች ይገምግሙ።

- ስለጎጂ ልማዳዊ ተግባራት መናገር መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ያዳመጡትን ምንባብ መልዕክቱን መረዳታቸውን ያረጋግጡ።
- በአበራሽ ላይ የደረሰው ነገር በሌሎች እናቶች ላይ እንዳይከሰት ከባለድርሻ አካላት ምን እንደሚጠበቅ መናገራቸውን ያረጋግጡ።
- የሥራ ማመልከቻ ደብዳቤ መጻፍ መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- የሃላፊ ጊዜን ተጠቅመው አንቀጽ መጻፍ መቻላቸውን ይገምግሙ።
- ለቃላት አውዳዊና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት መቻላቸውን ይገምግሙ።
- የሃላፊ ጊዜ ግሶችን በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም መቻላቸውን ያረጋግጡ።

# የተመረጡ የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ

## መልመጃ አንድ

### ሀ. አዳምጦ መረዳት

1. ሦስት
2. እናት ለመሆን በነበራት ጉጉት እና መውለድ እንደምትችል ለማረጋገጥ

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

### ለ. እውነት/ሀሰት

1. እውነት ምክንያቱም በመጀመሪያው፣ በሁለተኛው እና በሦስተኛው ልጆቿ መካከል ያለው የዕድሜ ልዩነት አንድ አንድ ዓመት ነው።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሁለት

### ሀ. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

1. አካላዊ፣ ማኅበራዊና ሥነልቦናዊ ጉዳቱ ከፍተኛ ስለሆነ ነው።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

### ለ. ሠንጠረዥ ማሟላት

| | |
|---|---|
| ያለዕድሜ ጋብቻ የሚፈጸምበት ምክንያቶች | **ለምሳሌ፡-** የኢኮኖሚ ችግር<br>• ዝምድናን ለማጠናከር<br>• ወላጆች ከመሞታቸው በፊት የልጅ ልጅ ለማየት እና ዘራቸው መቀጠሉን ለማረጋገጥ<br>• ጠለፋን መፍራት እና<br>• የመሳሰሉትን ሊያነሱ ይችላሉ |
| ያለዕድሜ ጋብቻ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች | **ለምሳሌ፡-** የጤና እክል<br>• የስነልቦና ጉዳት<br>• ማህበራዊ ጉዳት እና የመሳሰሉት |

**ሐ. ሠንጠረዥ ማሟላት**

| ማኅበረሰብ | ወላጅ | መንግሥት |
|---|---|---|
| ያለዕድሜ ጋብቻን እንደባህል አለመቀበል | ለራስ ክብር ሲሉ ልጆቻቸውን ያለዕድሜ አለመዳር | ከልካይ ህጎችን ማውጣት |

በዚህ ዓይነት ተማሪዎቹ የተለያየ ሀሳብ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

**መ. ባዶ ቦታ መሙላት**

1. ታዳጊ
2. ይጫወታል

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

## መልመጃ ሦስት

ሀ. ቃላትን በተቃራኒ ፍቺ ማዛመድ

1. ረ
2. ሰ
3. ሐ
4. ሸ
5. ሠ
6. መ
7. ሐ

## መልመጃ አራት

**ሀ. ሀላፊ ጊዜ ግሶችን ተጠቅመው ዓረፍተነገሮችን መመሥረት**

(የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊመሠርቱ ይችላሉ።)

**ለ. ሀላፊ ጊዜ ግሶችን የተጠቀሙ ዓረፍተነገሮችን መለየት**

1. 1ኛ፣ 3ኛ፣ 8ኛ፣ 10ኛ

**ሐ. ሀላፊ ጊዜ ግሶችን ተጠቅመው አንቀጽ መጻፍ**

(የተለያዩ አንቀጾችን ሊጽፉ ይችላሉ።)

# ምዕራፍ አሥር

# ሴቶችን ማብቃት (18 ክፍለጊዜ)

## 1. የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-

- አዳምጠው ፍላጎቶቻቸውን ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ይገልጻሉ፤
- ግለታሪክ ይጽፋሉ፤
- ተገቢ የአነባበብ ስልትን በመከተል ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ምንባብ ያነባሉ፤
- ቃላትን በምዕላድ ከፋፍለው ያሳያሉ፤
- በዓረፍተነገሮች ውስጥ ቀጥተኛ (ርቱዕ)ና ቀጥተኛ ያልሆኑ (ኢ-ርቱዕ) ተሳቢዎችን ይጠቀማሉ።

## 2. የትምህርት ይዘት

### 2.1. ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

- “የሴቶች እኩልነት” በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ ሲነበብ ማዳመጥ፤
- ሌሎች ተማሪዎች ስለሴቶች እኩልነት ሲናገሩ ማዳመጥ፤

### 2.2. ትምህርት ሁለት፡ መናገር

- ካዳመጡት ምንባብ የተረዱትን መልዕክት መናገር፤
- የሴቶች እኩልነትን ለማረጋገጥ ሊሠሩ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ሰዎችን በመጠየቅና በማንበብ ያገኙትን መረጃ መናገር፤

### 2.3. ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

- “ሴቶችን ማስተማር” የሚለውን ምንባብ ማንበብ፤
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን አንብበው መመለስ፤

### 2.4. ትምህርት አራት፡ መጻፍ

- ግለታሪክ መጻፍ፤

### 2.5. ትምህርት አምስት፡ ቃላት

- ቃላትን በምዕላድ መከፋፈል፤

### 2.6. ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው

- ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢዎችን መለየት፤

## 3. የማስተማሪያ ዘዴ

- ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎችንና ብልሃቶችን መጠቀም፤
- ከዝርዝር ወደአጠቃላይ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ከአጠቃላይ ወደዝርዝር የማስተማሪያ ስልቶችን መጠቀም፤
- ስለሴቶች እኩልነት  በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ፤
- ስለሴቶች እኩልነት በመቅረጸ ድምጽ ያሉ መረጃዎችን ወደክፍል በማምጣት እንዲያዳምጡ ማድረግ፤
- ሞዴል ግለታሪኮችን በክፍል ውስጥ በማቅረብ ተማሪዎቹ እንዲለማመዱ ማድረግ፤
- ቃላትን በፍሊፕ ቻርት በምዕላድ ከፋፍሎ በማሳየት እንዲለማመዱ ማድረግ፤
- እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎችንም መጠቀም ይችላሉ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህር! በዚህ ትምህርት ሥር ለማዳመጥ መነሻ የሚሆኑ የመልመጃ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸው፤ የሚሰጧቸውንም ምላሾች እንዳለ ይቀበሏቸው። ተማሪዎቹ የተለያዩ መልሶችን ሊሰጡ ስለሚችሉ ለማረም መሞከር አያስፈልግም። ምላሾቹን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ዋናው ትምህርት ይግቡ። በመጀመሪያ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው። በመጀመሪያው ንባብ ተማሪዎች በጸጥታ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። በመቀጠል በቦርድ ላይ የተሰጡትን የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች እያዳመጡ መሥራት እንዳለባቸው ይንገሯቸው። ከዚያም ባዳመጡት ምንባብ መሠረት የቀረቡትን መልመጃዎችና ተግባራት በተዕዛዞቻቸው መሠረት ያሠሯቸው። የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በቀጣይ ክፍለጊዜ የሚሠሩ ስለሆነ ከማሠራትዎ በፊት ሀሳቡን ለማስታወስ ምንባቡን በድጋሚ ያንብቡላቸው።

## የሴቶች እኩልነት

ሴቶች የማህበረሰቡ ግማሽ አካል ቢሆኑም በዓለም ካልተማሩ ሰዎች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛሉ። “ሴት ወደማጀት፣ ወንድ ወደችሎት” በሚል የተሳሳተ ብሂል ሴቶች ከቤት እንዳይወጡ ተደርገው ቆይተዋል። ወንዶች ለመማር፣ ለማወቅ፣ ለመመራመር፣ ለአመራር ወዘተ እንደተፈጠሩ ተደርጎ ይታመናል። ቤት ማጽዳትና ማስዋብ፣ ምግብ ማብሰል፣ ልጅ መንከባከብ ወዘተ. ደግሞ የሴቶች ሥራ እንደሆኑ ይታሰባል። በመሆኑም ወንዶች ወደትምህርትቤት ሲሄዱ ሴቶች ለእነሱ ብቻ ባልተሰጡ የቤት ውስጥ ሥራዎች ይጠመዳሉ። ስለሆነም የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዓለማቀፋዊ ስምምነቶች በተለያዩ ጊዜያት ተደርገዋል። ለምሳሌ እ.አ.አ. በ1981 ሴቶችና ወንዶች እኩል የመማር መብት እንዳላቸው ተወስኗል። እንዲሁም እ.አ.አ. በ1990 ጾታ ሳይለይ ሁሉም ሕፃናት እኩል የመማር መብት እንዳላቸው ተደንግጓል።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ጾታ ሳይለይ ሁሉም ሕፃናት እኩል የመማር መብት እንዳላቸው የተደነገገው መቼ ነው?
2. "የሥርዓተጾታን እኩልነት ማረጋገጥ" ሲል ምን ማለት ይመስላችኋል?

በዚህም መሠረት እ.አ.አ. በ1995 ሥርዓተትምህርቶች ሁለቱንም ጾታዎች አማክለው እንዲዘጋጁና ሴቶች ቢማሩ የሚኖራቸውን ሚና እንዲያካትቱ ተደንግጓል። ይህንንም በማጠናከር እ.አ.አ. እስከ2005 ሁሉም ሕፃናት በተለይ ሴቶች በነፃ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲማሩ ግብ ተጥሏል። በተጨማሪም እ.አ.አ. እስከ2015 ድረስ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥ ስምምነት ላይ ተደርሷል። ከዚህ አኳያ ሀገራት በሥርዓተጾታ ላይ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለመለወጥና ለማስተካከል ከፍተኛ ጥረቶችን አድርገዋል። በዚህም ምክንያት ትምህርትቤት በመግባትና ትምህርት በመጨረስ ረገድ በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነቶች ቢኖሩም መጠነኛ መሻሻል ታይቷል። እ.አ.አ. ከ1990 ዓ.ም. ጀምሮ በትምህርት መስክ በሁሉም የዓለም ክፍሎች አጠቃላይ የሴቶች ተሳትፎ መጠን 10 በመቶ ጨምሯል። በአብዛኞቹ የዓለም ክፍሎች ደግሞ በመሠረታዊ ትምህርት የሴቶች የተሳትፎ መጠን ከወንዶች ጋር ተቀራራቢ ሆኗል። ይህም ሆኖ ግን አሁንም በትምህርት መስክ ያለውን የጾታ ልዩነት ለማስወገድ ተጨማሪ ጥረቶች ያስፈልጋሉ።

በአጠቃላይ ሴቶችንና ወንዶችን እኩል የማስተማር ልምድ በሁሉም የዓለም ክፍሎች የዳበረ አይደለም። በዚህ የተነሳ የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ከወንዶች እጅግ ያነሰ ነው። ይህም የሀገርን ዕድገት በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳል። በማንኛውም መስክ ሀገራዊ ዕድገት ለማምጣት የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው። ስለሆነም የተዛቡ ማህበራዊ አመለካከቶችን በማስወገድ ሴቶችንና ወንዶችን እኩል ማስተማር ያስፈልጋል።

(ሲዳ። 2010። ኢዱኬሽን ጀንደር ኢኳሊቲ። ገጽ1-7 እና ኦክስፋም ኢትዮጵያ ካንትሪ ፕሮፋይል። 2013። ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

### መልመጃ አንድ

በመልመጃ አንድ፤ ሁለት ትዕዛዞች ሥር ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች ቀርበዋል። አንደኛው በቃል የሚመልሷቸው ጥያቄዎች ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ ሠንጠረዥ በመሙላት የሚመልሷቸው ናቸው። ስለዚህ ጥያቄዎቹን ተማሪዎቹ በተሰጧቸው ትዕዛዞች መሠረት እንዲመልሱ ወይም እንዲሠሩ ያበረታቷቸው። የተሳሳተ መልስ ከሰጡ በምንባቡ መሠረት ያስተካክሏቸው።

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት አዳምጠው ጽብረቃ ለማካሄድ የሚያስችላቸው ተግባራት ቀርበዋል። ስለዚህ ሀሳቦቹን መሠረት በማድረግ ንግግር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።

## ተግባር አንድ

በዚህ ተግባር ሥር ንግግር ለማድረግ መነሻ የሚሆኑ ሁለት ሀሳቦች ቀርበዋል። አንደኛው ካዳመጡት ምንባብ የተረዱትን መልዕክት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ የሚጠይቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የሴቶች እኩልነትን ለማረጋገጥ ሊሠሩ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ሰዎች በመጠየቅና በማንበብ ያገኙትን መረጃ በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት ንግግር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት ሥር "ሴቶችን ማስተማር" የሚል ምንባብ ቀርቧል። ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያነቡ የቅድመንባብ ጥያቄዎች ተሰጥቷል። ጥያቄዎቹን ይጠይቋቸውና እንዲመልሱ ያነሳሷቸው፤ የሚሰጡትንም መልሶች ይቀበሏቸው። ምንባቡን ሲያነቡ የማያውቋቸውን ቃላትና ሀረጋት እየጻፉ ሀሳቡንም እየተረዱ በየግላቸው ድምፅ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ይንገሯቸው። ከዚያም ተማሪዎች ምንባቡ ላይ ተመሥርተው የቀረቡትን መልመጃዎች በትዕዛዞቹ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሁለት

በመልመጃ ሁለት ሥር በሦስት የተለያዩ ትእዛዞች ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጀመሪያው ተማሪዎች ባነበቡት ምንባብ መሠረት በቃል መልስ የሚሰጡበት ሲሆን ሁለተኛው ባነበቡት ምንባብ መሠረት መረጃዎችን በሠንጠረዥ ለይተው እንዲያስቀምጡ የሚጠይቅ ነው። ሦስተኛው ደግሞ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ በመስጠት ዓረፍተነገር እንዲመሠርቱባቸው የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም ተማሪዎቹ ለጥያቄዎቹ ተገቢ መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፤ የተሳሳቱ ምላሾች ከሰጡ ደግሞ ትክክለኛ የሆኑትን መልሶች በመንገር ተማሪዎቹን ይርዷቸው።

## ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ተግባር ሥር ግለታሪክ እንዲጽፉ የሚያስችላቸው ማስታወሻ እና ተግባራት ቀርበዋል። በመሆኑም ለተግባራቱ በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት እንዲሠሩ ያግዟቸው።

## ተግባር ሁለት

በዚህ ተግባር ሥር ሁለት ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው በተሰጣቸው ምሳሌ መሠረት የራሳቸውን ግለታሪክ እንዲጽፉ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የጻፉትን ግለታሪክ ተለዋውጠው ርስበርስ እንዲተራረሙ የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ሥር ቃላትን በምዕላድ እንዲከፋፍሉ የሚጠይቅ መልመጃ ቀርቧል። ስለዚህ መልመጃውን በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ያሠሯቸው።

## መልመጃ ሦስት

በዚህ መልመጃ ሥር ቃላትን በምዕላድ በመከፋፈል መልስ የሚሰጡባቸው ናቸው። ስለሆነም በትዕዛዙ መሠረት እንዲሠሩ ያድርጉ፤ ለመልሶቻቸውም ማስተካከያ ይስጧቸው።

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ሥር ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢዎች ለመለየት የሚያስችላቸው መልመጃ ቀርቧል። ስለሆነም የቀረቡትን መልመጃዎች በተሰጡ ትዕዛዞች መሠረት እንዲሠሩ ያድርጉ።

## መልመጃ አራት

በዚህ መልመጃ ሥር ሦስት ትዕዛዞች ቀርበዋል። አንደኛው ከተሰጡ ዓረፍተነገሮች ውስጥ ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢዎችን ለይተው እንዲያመለክቱ የሚጠይቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ቀጥተኛ ተሳቢዎችን በመጠቀም ዓረፍተነገሮች እንዲመሠርቱ የሚጠይቅ ሲሆን ሦስተኛው ኢ.ቀጥተኛ ተሳቢዎች በመጠቀም ዓረፍተነገር እንዲመሠርቱ የሚጠይቅ ነው። ስለዚህ ተማሪዎቹ ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢዎችን በጽሑፋቸው ውስጥ እንዲጠቀሙ ያድርጉ፤ ማስተካከያ በመስጠትም ይርዷቸው።

### ግምገማ

ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መረዳታቸውን በሚከተሉት ነጥቦች ይገምግሙ።

- ስለሴቶች እኩልነት መናገር መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ያዳመጡትን ምንባብ መልዕክቱን መረዳታቸውን ይገምግሙ።
- በተማሩና ባልማሩ ሴቶች መካከል ያለውን የአኗኗር ዘይቤ ልዩነት መናገራቸውን ይገምግሙ።
- ግለታሪክ መጻፍ መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ቃላት በምዕላድ መከፋፈል መቻላቸውን ይገምግሙ።
- ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳቢዎችን በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም መቻላቸውን ያረጋግጡ።

# የተመረጡ የመልመጃ ጥያቄዎች መልስ

## መልመጃ አንድ

### ሀ. አዳምጦ መረዳት

1. "ሴቶች ለእነሱ ብቻ ባልተሰጡ የቤት ውስጥ ሥራዎች ይጠመዳሉ።" ሲባል ሥራዎች በጾታ የተከፋፈሉ ባይሆኑም በማኅበረሰቡ አመለካከት ግን ቤት ማጽዳት፣ እንጀራ መጋገር፣ ወጥ መሥራት፣ ልጆች መንከባከብ፣ ወዘተ. ያሉት ለሴት ብቻ የተሰጡ ተደርገው ስለሚቆጠሩ እነዚህን ሥራዎች ሲሰሩ ይውላሉ ለማለት ነው።

(ቀሪውን ጥያቄ በዚህ መንገድ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

### ለ. ሠንጠረዥ መሙላት

| ዓመተምህረት | ድንጋጌዎች |
|---|---|
| ለምሳሌ፡1981 | ሴቶች ከወንዶች እኩል የመማር መብት እንዳላቸው ተደነገገ። |
| 1990 | ጾታ ሳይለይ ሁሉም ሕፃናት እኩል የመማር መብት እንዳላቸው ተደንግጓል። |
| 1995 | ሥርዓተትምህርቶች ሁለቱንም ጾታዎች አማክለው እንዲዘጋጁ ተደንግጓል። |
| 2005 | ሁሉም ሕፃናት በተለይ ሴቶች በነፃ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲማሩ ግብ ተጥሏል። |

## መልመጃ ሁለት

### ሀ. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

1. የራሳቸውን የተለያየ ሀሳብ ሊሰነዝሩ ይችላሉ።
2. የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን በአግባቡ በመጠቀም ነው።

(ቀሪውን ጥያቄ ያሠሯቸው። ግብረመልስም ይስጧቸው።)

### ለ. ሠንጠረዥ መሙላት

ተማሪዎቹ የተለያየ ሀሳብ ሊሰጡ ይችላሉ። ሀሳባቸውን ይቀበሏቸው፤ ግብረመልስም ይስጧቸው።

### ሐ. ለቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት

የተለያየ አውዳዊ ፍቺ ሊሰጡና የተለያየ ዓረፍተነገር ሊመሠርቱ ይችላሉ።

# መልመጃ ሦስት

## ሀ. ቃላትን በምዕላድ መከፋፈል

| ተ.ቁ | ቃላት | ምዕላዶች |
|---|---|---|
| 1 | ምሳሌ፡ እንደተናገሩት | እንደ-ተናገር-ኡ-ት |
| 2 | በመንከባከባቸው | በ-መንከባከብ-ኣቸው |
| 3 | እንደለበሳችሁ | እንደ-ለበስ-ኣችሁ |
| 4 | ቤተመንግሥታችን | ቤት-ኧ-መንግስት-ኣችን |
| 6 | በወንበራቸው | በ-ወንበር-ኣቸው |
| 7 | ልብሶቻችንን | ልብስ-ኦች-ኣችን-ን |
| 8 | ቤቴን | ቤት-ኤ-ን |
| 9 | ሀገራችንን | ሀገር-ኣችን-ን |
| 10 | ትውልዴን | ትውልድ-ኤ-ን |

ለ. የተለያዩ ቃላትን አምጥተው በምዕላድ ሊከፋፍሉ ይችላሉ።

# መልመጃ አራት

ሀ. ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተሳቢዎችን መለየት

1. እሱ መጽሓፉን ቀደደ። (መጽሓፉን = ቀጥተኛ)
2. ሰውዬው በዱላ ውሻውን መታው። (በዱላ= ኢቀጥተኛ፤ ውሻውን =ቀጥተኛ)
3. መጽሓፍ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠ። (ጠረጴዛ = ኢቀጥተኛ)
4. እሷ መስኮቱን ከፈተች። (መስኮቱን = ቀጥተኛ)
5. እሷ በመኪና ሄደች። (በመኪና = ኢቀጥተኛ)
6. ናሲሴ ለልጇ ልብስ ገዛች። (ለልጇ= ኢቀጥተኛ፤ ልብስ = ቀጥተኛ)

# አማርኛ እንደ አፍመፍቻ ቋንቋ የ6ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት

## መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ በትምህርት አሰጣጥ ፈጣንና መሻሻል በታየበት ሁኔታ እየሰራች ነው። ልዩ ትኩረት የተሰጠው "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለውን ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" ላይ ነው። ይኸውም ለ21ኛው ክፍለ ዘመን እድገት እንደመሳሪያ ሆኖ በብቃት ህብረተሰቡን ወደ ፊት የሚያራምድ ነው። ይህንን ግብ ለማሳካት ትምህርት ሚንስቴር የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ምርምሮችን በማድረግ አዲስ ስርዓተ ትምህርትን ቀርጿል። በዚህም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት መሳሪያዎቹ (የይዘት ፍሰት፣ አነስተኛ የመማር ብቃትና መርሀትምህርት) በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ስርአተ ትምህርት ማእቀፍ ውስጥ ተመስርተው እንዲዘጋጁ ተደርገዋል። እነዚህ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት መሳሪያዎች ዋና መነሻቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ልህቀትን ለማሻሻል ሲሆን በአውድ የተደገፈ፣ በህጻናት እድገት ላይ በተደረገው የምርምር ማስረጃና በመማር ላይ የተመሰረተ ትምህርታዊ ስኬታማነትን እንዲያረጋግጡ ተደርገው ተቀርፀዋል። በአውዱ የተሰጡት መነሻ ልምምዶችም የተማሪውን መማር የመጨረሻ ግብ የሚያሳድጉ ናቸው ተብሎ ይታሰባል። የስርዓተ ትምህርት መሳሪዎች በዋናነት እንዲቀረፁ የተደረጉት የመማር ውጤት፣ ብቃት፣ ይዘት፣ የመማር ስልቶች፣ ምዘናና ለእያንዳንዱ ይዘት ጊዜ በመስጠት ነው።

መርሃ ትምህርቱ የተለያዩ አገር በቀል እውቀቶችን፣ ዋና ዋና ክሂሎችን፣ ለህይወት አስፈላጊ የሆኑትንና ብርቱ ብሄራዊ ጉዳዮችንና ብቃቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅቷል።

ይህም በብሄራዊና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ብቁ ዜጋ ለማፍራት ታስቦ የተሰናዳ ነው። የይዘቱ ፍሰትም ከቀላል ወደ ውስብስብ፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሚሄድ ሆኖ ተማሪዎቹ አውዳዊ ይዘቱን እንዲረዱ የሚያስችል ነው። መልመጃዎቹ ተማሪ ተኮር የሆኑ፣ አብዛኛውን እድል ለተማሪዎች የሚሰጡ፣ የታሰበውን የቋንቋ ክሂል ተለማምደው እንዲያሳድጉ የሚያስችሉ ሆነው በደረጃቸው የቀረቡ ናቸው።

በዚሁ መሰረት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በክልሉ ለሚገኙ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ ለፈቱ ተማሪዎች ይህን በትምህርት ሚኒስቴር የቀረበ ስርዓተ ትምህርት ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ አስማምቶ አቅርቦታል።

### የአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ግቦችና አላማዎች

#### የአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ግቦች ፡-

- ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያለውን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በስኬታማነት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎቹ ቀጥለው ያሉትን ግቦችና አላማዎች እንዲያሳኩ ይጠበቃል።

# ግቦች

- የመሰረታዊ ፊደላትን ክሂል ማበልጸግ የተማሪውን አእምሮታዊ፣ስሜታዊና ማህበራዊ ክሂሎችን ለማሳደግ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤
- ተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎትና ስነልሳናዊ እውቀት ማስተዋወቅ ለተግባቦት ብቃት ማዳበር ስለሚያግዛቸው ሀሳባቸውንና ስሜታችውን በተለያዩ አውዶች ውስጥ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፤
- ተማሪዎቹን አገር በቀል እውቀትና እሴቶችን እንዲያውቁ ስለሚያደርጋቸው በተለያዩ ማህበራዊ አውዶች ውስጥ እንዲጠቀሙባቸው ያስችላቸዋል።

# አላማዎች

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማርና የመማር አበይት አላማዎች፡-**

- ➢ መሰረታዊ ትምህርትን በማዳበር ተማሪዎች ለወደፊት የትምህርት ግባቸው ዝግጁ እንዲሆኑ ጽናት ይሰጣቸዋል፤
- ➢ የቋንቋውን ዋና ዋና ክሂሎች መረዳት የተግባቦት ችሎታቸውን ለማሳደግ እና ሀሳባችውንና ስሜታቸውን ውጤት ባለው መንገድ ለመግለጽ ይረዳቸዋል፤
- ➢ የቋንቋውን ንዑሳን ክሂሎች ማወቅ የተግባቦት ችሎታቸውን ለማዳበር እንደሚረዳቸው እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል፤
- ➢ ከሳይንሳዊ ምርምር የተገኙትን የቋንቋና የስነልሳን ባህሪያት እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፤
- ➢ የቋንቋ አጠቃቀምን በትምህርት፣ በማህበራዊ ኑሮና በምጣኔ ሀብት ሁነቶች ውስጥ እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፤
- ➢ የአገር በቀል ቋንቋ ስልቶችን በተለያዩ የቋንቋ ይዘቶች በማቅረብ እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል።

# ራዕይና እሴቶች

## ራዕይ

የአፍ መፍቻ ቋንቋ መማርና ማስተማር ለአለም ቋንቋዎች ሁሉ ዋጋ ይሰጣል ተብሎ ስለሚጠበቅ እያንዳንዱ ሰው በተለይም ህጻናት ቋንቋውን መናገር ብቻ ሳይሆን መማር በመቻል ያንን ቋንቋ በቀላሉ ይረዳሉ። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጠንካራ መሰረቶች

የሚኖሩ ከሆነ ተማሪዎች በተሻለ መንገድ ስርዓተ ትምህርቱን እየተረዱ እንደዚሁም አዎንታዊ አመለካከት ኖሯቸው ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ። ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከህጻንነታቸው ጀምሮ ጠበቅ አድርገው ማወቃቸው አስፈላጊ በመሆኑ በየክፍል ደረጃው የተሻለ ጥረት በማድረግ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ።

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የህጻናት አእምሮ ብስለትን በማሳደግ የቋንቋ ክሂሎችን፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶችንና ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር ይረዳቸዋል። ይህን እሳቤ ውስጥ በማስገባት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ተምረው ያለፉ ኢትየጵያዊ ተማሪዎች በሰላምና በመተሳሰብ አብሮ በመኖር ፡-

- ብቃት ያለው የቋንቋ ክሂል ባለቤት፣ ባህልንና ማንነትን አክባሪ፣የማሰብና የመፍጠር ባለቤት፣ በራስ የሚተማመኑ፣ ችግር ፈቺዎች፣ ትጉኃን፣ ትኩረት ሰጪዎች፣ ምክንያታዊያን ተባባሪና ራስን በመስጠት የሚሰሩ ይሆናሉ፤

# እሴቶች

እሴቶች አስፈላጊና ፍትሃዊ ስለሆኑ ነገሮች ያሉን እምነቶች ናቸው። እሴቶች ድርጊታችንንና ውሳኔያችንን ይመራሉ፤ ስለዚህ ይህ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት የተዘጋጀው ጽሁፍ ተማሪዎቹ፡-

አገር በቀል እወቀቶችን አክባሪና ተጠቃሚ፣ የህብረተሰቡን የግጭት አፈታት ባህሎችን የሚተገብሩ፣ የስርዓተ ጾታ እኩልነትን ተግባራዊ የሚያደርጉ፣ የመረዳዳት መንፈስ ያላቸው፣ የመቻቻል ባህል የተላበሱ፣ ብሄራዊና አለማቀፋዊ ቅርስ የሚንከባከቡ፣ በልዩነት ውስጥ አንድነት የሚቀበሉ፣ እርስ በእርስ የሚከባበሩ፣ ጠንክሮ የመሥራት ባህል ያላቸው፣ በላቀ ሁኔታ የሚያስቡ፣ የፈጠራ ችሎታን የተላበሱ፣ ችግር ፈቺዎች፣ ስለአካባቢ ጥበቃ የሚያስቡ እንዲሆኑ የሚያበረታታ መሆን አለበት።

# የአንደኛ መንፈቀ አመት

## ምዕራፍ አንድ፣ ባህላዊ አልባሳት (18 ክፍለ ጊዜ)

### የሚጠበቀው ውጤት

ይህንን ምዕራፍ ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ዓረፍተ ነገር ለመመስረት የሚያስችሉ የቃላት አፃፃፍ ህጎችን አዳምጠው ይገልፃሉ፤
- አቀላጥፎ ማንበብን ይለማመዳሉ፤
- በአረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ ውስብስብ ቃላትን ትርጉም ይሰጣሉ፤
- ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀ ፅሑፍ ውስጥ የሚገኝ ፍቺን ለመረዳት ተገቢ ንበትንና ስርዓት ነጥቦችን ይጠቀማሉ፤
- ቃላትን እየነጠሉ ያነባሉ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| • ፅሑፉን አዳምጠው መልዕክቱን ይገልፃሉ።<br>• በማንበብ አቀላጥፎ ማንበብን ይለማመዳሉ።<br>• ከሚቀርበው ምንባብ ውስጥ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ይሰጣሉ።<br>• የተሰጠ ሀሳብ መነሻ በማድረግ ዓረፍተ ነገር ይፅፋሉ።<br>• የተፀውዖንና የወል ስሞችን አረፍተ ነገር ለመመስረት ይጠቀማሉ። | • ማዳመጥና መናገር<br>• ማንበብ<br>• ቃላት<br>• መፃፍ<br>• ሰዋስው | ተማሪዎች የቃላት መዋቅርን ወይም የሆሄያት አሰዳደርን ያነፃፅራሉ። ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-<br>• ተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን ማወዳደር<br>• በመዋቅር ወይም በሆሄያት አደራደራቸው የተዘረዘሩ ቃላትን መለየት<br>• ቃላትን በጋራ መዋቅራቸው ወይም ስደራ አማካኝነት ማቧደን<br>• ተማሪዎች ቃላትን በቀረበላቸው መዋቅር ወይም ስደራን መሰረት በማድረግ እያሰቡ መዘርዘር<br>• የቃላትን ስነምዕላዳዊ መዋቅርን መሰረት ያደረገ መመሪያና ተግባራት | • ተማሪዎች የቀደመውን ትምህርት መሰረት አድርገው የቀረቡ ጥያቄዎችን መመለስ የተማሩትን ማጋራት<br>• -መምህር ይህንን መረጃ የወቅቱን ትምህርት አካሄድ ለመወሰን ይጠቀሙበታል።<br>• አቅርቦት ተማሪዎች እያጎለበቱ ያሉትን የቃላት እውቀት ለመምህር ወይም ለክፍሉ በተግባር እንዲገልጡ/ እንዲያሳዩ እድል ይሰጧቸዋል።<br>• ተማሪዎች የቃላት እውቀታቸውን ማጎልበት፣ የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት |

# ምዕራፍ ሁለት፤

# ዝነኛ አትሌቶች (18 ክፍለ ጊዜያት)

## የሚጠበቀው ውጤት

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተከታተሉ በኋላ፡-

- ✓ ቃላትን ከምዕላዶች ይለያሉ፤
- ✓ ምዕላዶችን በማጣመር ቃላት ይመሠርታሉ፤
- ✓ የተለያዩ ምንባቦችን በማንበብ ዋናውን ሀሳብ ይናገራሉ፤
- ✓ በክፍል ደረጃው የቀረበ ምንባብ ፍቺን ለመረዳት ድምፀትን በስርዓተ ነጥቦች ደረጃ ይጠቀማሉ፤
- ✓ አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- ✓ ጥቅል ስሞችንና ተውሳከግሶችን ይለያሉ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• በቡድን ውይይት ይሳተፋሉ።<br>• በክፍል ደረጃው ትክክለኛነትን በንባብ አማካኝነት ይለማመዳሉ።<br>• አጭር አንቀፅ ይፅፋሉ<br>• የይዘትና አዳዲስ ቃላትን,ያስተዋውቃሉ/ ይወያያሉ።<br>• የተማሯቸውንና ከፍ ያለ ውስብስብነት ያላቸውን የቀለማት መዋቅሮችንና ምዕላዶችን በማጣመርና በመነጠል ቃላትን ይለያሉ። | • ማዳመጥና መናገር<br>• ማንበብ<br>• ቃላት<br>• መፃፍ<br>• ሰዋስው<br>• ሰዋስው | • የቡድን ውይይት፡<br>- ተማሪዎች በማዳመጥና በቡድን ውይይት በመሳተፍ ቀጥሎም ሰዎች ስለሚከውኑት በመናገር ግንዛቤያቸውን ማዳበር<br>• ሰዎች ንፅህናን ለመጠበቅ የት እንደሚሄዱና ምን እንደሚያደርጉ የሚገልፅ ዕለታዊ ዕሑፍን ማንበብ<br>• ተማሪዎች ሰዎች በክፍል ውስጥ ምን እንደሚከውኑ መናገር<br>• ተማሪዎች በጥንድ በመሆን የተጓደለ መረጃ ያላቸውን ተግባራት ማሟላት<br>• አንድ ተማሪ ንፅህና መጠበቅን በተመለከተ በምልክት መግለፅ፣ በምልክት የተገለጸውን መገመት | • **አካላዊ ምላሽ**<br>ተማሪዎች ለጥያቄዎች አካላዊ እንቅስቃሴን በመጠቀም በተናጠል ምላሽ መስጠት። አውራጣትን ማውጣት/ ማውረድ፣ ቡጢ መጨበጥ መዘርጋት፣ ጣትን እያወጡ ማሳየት የመሳሰሉት መልስን ሊያመለክቱ የሚችሉ ናቸው።<br>• **መደበኛ ያልሆነ ቁጥጥር**<br>መምህር ፅሑፍን ማንበብ የመሰሉ ስራዎችን ለተማሪዎቹ በመስጠትና ክፍሉ ውስጥ በመዘዋወር መደበኛ ባልሆነ መልኩ ክትትል ማድረግ |

# ምዕራፍ ሦስት፡

## ቃላዊ ግጥሞች (18 ክፍለ ጊዜያት)

## የሚጠበቁ ውጤቶች፡

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- አዳዲስ የተማሩትን ቃላት አዳምጠው ጥቅም ላይ ያውላሉ፤
- ግጥምን አቀላጥፈው ያነባሉ፤
- ግጥምን ይጽፋሉ፤
- በዓረፍተነገሮች ውስጥ ቅንፍና ህዝባርን ይጠቀማሉ፤
- የተማሩትን አዳዲስ ቃላት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚያነቧቸው ቃላዊ ግጥሞች ውስጥ ይጠቀማሉ፤
- የጊዜ ተውሳከግሶችን ትለያላችሁ፤
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• አዳምጠው ተመሳሳይ ቃላዊ ግጥሞችን ይናገራሉ።<br>• ግጥምን አቀላጥፈው ያነባሉ።<br>• የግጥሙን ጭብጥ ይፅፋሉ።<br>• ቅንፍንና እዝባርን በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ይጠቀማሉ።<br>• ከተለያዩ ቃላት መካከል ተቃራኒ ቃላትን ለይተው ያወጣሉ።<br>• በአረፍተ ነገር ምስረታ ውስጥ ያሉ የጊዜ ተውሳከ ግሶች ይለያሉ፣ ይጠቀማሉ። | • ማዳመጥና መናገር<br>• ማንበብ<br>• ቃላት<br>• መፃፍ<br>• ሰዋስው | • **ምሪታዊ ፅሑፍ**<br>• መምህሩ የአንድ አይነት አፃፃፍ መንገድን የሚያሳይ ናሙና ወይም ቅርፅ ለተማሪዎቹ፣ ለምሳሌ ጅምር አረፍተ ነገር ወይም የደብዳቤ ቅርፅ ማቅረብ<br>• ብቁ የማህበረሰብ ፀሐፊዎችን መፍጠር፤ (መምህርቷ/ሩ ፅሑፉን/ኗን በሞዴልነት በማጋራት)<br>• በፅሑፍ ስራዎች ውስጥ ተማሪዎቹ የመፃፍ አማራጮችን እንዲያገኙ ማድረግ<br>• ተማሪዎቹ እንደፀሐፊዎች እንዲተጋገዙ እንዲሰሩ ማበረታታት<br>• ተማሪዎች ግብረ መልስን እንዲሰጡና እንዲቀበሉ እድል መስጠት | • **ፊትን ወደ ጓደኛ ማዞርና ማውራት**<br>በንባብ ወቅት ፍጥነትን፣ ትክክለኛነትንና ተገቢ አገላለፅን ወይም ለዕህፈት ዝግጅት የሚረዱ ሀሳቦች ላይ ለመወያየት አንድ ወይም ሁለት ተማሪዎች አንዳቸው ላንዳቸው አንቀፅ ማንበብ<br>• **መቁጠሪያዎች**<br>በተሰጠ ፕሮጀክት ላይ የተማሪዎችን አፈፃፀም ለመገምገም የመስፈርቶችን ጠረጴዛ መጠቀም። ለምሳሌ መስፈርቱ ተለጣጣቂነትን ወይም አደረጃጀትን እንዲሁም ትክክለኛነትን የሚያካትት ይሆናል። ከተማሪዎቹ ምን እንደሚጠበቅ አስቀድሞ ግልፅ ሊደረግላቸው ይገባል። |

# ምዕራፍ አራት፡

# ዘመናዊ ግብርና (18 ክፍለ ጊዜያት)

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ፡-

- ✓ አዳምጠው ቃላዊ ምላሽ ይሰጣሉ፤
- ✓ አመዛዛኝ አንቀፅን ይፅፋሉ፤
- ✓ ፍቺን ለመስጠት አብሮ ሂያጅ ቃላትን ይጠቀማሉ፤
- ✓ ጊዜ አመልካች ተውሳከግሶችን በመጠቀም አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• አዳምጠው የፅሑፉን መልዕክት በተመለከተ የቃል ዘገባ ያቀርባሉ።<br>• አንብበው አዳዲስ የቃላት እውቀቶችን ይገነባሉ።<br>• የቃላት አብሮ ሂያጆችን በመጠቀም ለቃላት ፍቺን ይሰጣሉ።<br>• አመዛዛኝ አንቀፅ ይፅፋሉ። | • ማዳመጥና መናገር<br>• ማንበብ<br>• ቃላት<br>• መፃፍ<br>• ሰዋስው<br>• ሰዋስው | • የተለያዩ የፅሑፍ አይነቶችን በየጊዜው ማንበብ ዳራዊ ዕውቀትን ይገነባል፤ በተዘዋዋሪም የፅሕፈት ክሂል እንዲሻሻል ይረዳል።<br>• **መከታተል**<br>  • ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የሚያጋጥሟቸውን ቃላት ወይም ፅንሰ ሀሳቦች መረዳት ካቃታቸው ለተጨማሪ ውይይት ለመጋበዝ እንዲያመች ቃላቱን ለይቶ መያዝ<br>• መምህር ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ተማሪዎቹ በጥንድ ወይም በቡድን ይመልሷቸው ዘንድ ማስተዋወቅ<br>• ተማሪዎቹ በዝምታና ራሳቸውን ችለው በማንበብ ለጥያቄዎቹ የሰጧቸውን መልሶች ማረጋገጥ/እርማት መስጠት | • **ምሪታዊ ክለሳ፡** የቀደመውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት መነሻ በማድረግ አዳምጠው ጥያቄዎችን መመለስ የተማሩትን ማጋራት፤ መምህር ይህንን መረጃ የዕለቱን ትምህርት አካሄድ ለመወሰን ይጠቀሙበታል<br>• **ካርዶችን ማውጣት፡** ተማሪዎች የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ካርዶች በማውጣት ለጥያቄዎች የተለያዩ ምላሾችን መስጠት (ለምሳሌ እስማማለሁ/ አልስማማም ወይም እውነት/ሐሰት ብሎ መመለስ)<br>ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን በመሥራት የምንባቡን ጭብጥ መገመት |

# ምዕራፍ አምስት፥

## ቱሪዝም (18 ክፍለ ጊዜያት)

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተከታተሉ በኋላ፡-

- አዳምጠው ቃላትን ወደ ምዕላዶች መነጣጠልን ይተገብራሉ፤
- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ሀላፊ ጊዜን በመጠቀም አንቀፅ ይጽፋሉ፤
- ድህረ ቅጥያዎችን ይጠቀማሉ፤
- የተዘጋጀን ፅሑፍ ለመረዳት ራስመር ብልሃቶችን ይጠቀማሉ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• አዳምጠው ቃላትን በምዕላድ ደረጃ መነጠልን ይተገብራሉ።<br>• አንብበው የፅሑፉን ዋና ሀሳብ ያብራራሉ<br>• ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ።<br>• በሀላፊ ጊዜ አንቀፅ ይፅፋሉ።<br>• ድህረ ቅጥያዎችን በመለየት በተገቢው ቦታቸው ይጠቀማሉ። | • ማዳመጥና መናገር<br>• ማንበብ<br>• ቃላት<br>• መፃፍ<br>• ሰዋስው | • ለፅህፈት ብቁ የሆኑ ማህበረሰብን መፍጠር- መምህርቷ/ሩ ለመፃፍ ተምሳሌት በመሆንና ፅሑፏ/ፉን በማጋራት መሳተፍ<br>• ድምፅን ከፍ ተደርጎ ከሚነበበው ፅሑፍ ጋር ትስስርን መፍጠር<br>• ድምፅን ከፍ አድርጎ የተነበበውን ፅሑፍ በራሳቸው ቃላት መልሶ መዘገብ<br>• ተማሪዎቹ እንደ ፀሐፊዎች ሆነው ትብብር እንዲያደርጉ ማበረታታት- ግብረ መልሶችን እንዲሰጡና እንዲቀበሉ የሚያስችል ዕድልን ማቅረብ<br>• ነገሮችን ግልፅ ማድረግ- ያነበቡትን በተመለከተ አደናጋሪ ጉዳዮች ሲገጥሟቸው ተጨማሪ ማብራሪያ ከመጠየቅ እንዳይታቀቡ ማትጋት | • **ምልከታ** ተማሪዎች ክፍለ ጊዜው እየተካሄደ ወይም ክፍለ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ በቡድን ወይም በተናጠል ሲሰሩ አጫጭር ማስታወሻዎችን መፃፍ። መምህርቷ/ሩ በውስን የመማሩ ገፅታ ላይ ብቻ ፅብረቃ ማካሄድ<br>• **አቅርቦት** ተማሪዎች ግንዛቤያቸውን ለመምህር ወይም ለክፍሉ ወይም ለክፍሉ የሚያቀርቡበት እድል አላቸው።<br>• **የጥያቄ - መልስ** ግንኙነት- ድህረ ምንባብ ጥያቄዎች አራቱን አይነቶች ጨምሮ፥<br>- በትክክል እዚያው (ምላሹ በአንደኛው አረፍተ ነገር ውስጥ ይገኛል) |

# ሁለተኛው መንፈቀ አመት
# ምዕራፍ ስድስት፣
# ፀረ አደንዛዥ እና ንጥረ ነገሮች (18 ክፍለ ጊዜያት)

## የሚጠበቁ ውጤቶች

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችን ከተከታተሉ በኋላ ተማሪዎች፡-

- ለንባብ ተግባራት ተገቢ የሆኑ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መርጠው ይተገብራሉ፤
- የፅሑፍን መዋቅር ይለያሉ፤
- ለአንግዳ ቃላት ከአውዱ በመነሳት ፍቺ ይሰጣሉ፤ ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ጅምር አንቀጽ አሟልተው ይጽፋሉ፤
- ስለአንድ ርዕሰ ጉዳይ በሚገልፁበት ጊዜ መሸጋገሪያ (አያያዥ) ቃላትን (ሐረጋትን) ይጠቀማሉ፤
- ተውላጠስሞችን በዓረፍተነገር ውስጥ ይጠቀማሉ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• ፅሑፍን አዳምጠው በጉዳዩ ላይ ውይይት ያደርጋሉ።<br>• ፅሑፍን አንበብበው ያገኙትን መልዕክት ከእውናዊ ህይወታቸው ጋር ያዛምዳሉ።<br>• ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ያላቸውን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይጠቀማሉ።<br>• አንቀፅ ይጽፋሉ።<br>• ተውላጠ ስሞችን በመጠቀም ዓረፍተነገሮች ይመሰርታሉ። | • ማዳመጥና መናገር<br>• ማንበብ<br>• ቃላት<br>• መፃፍ<br>• ሰዋስው<br>• ሰዋስው | • **ግልፅ ማድረግ፡** - ተማሪዎች በንባብ ወቅት የገጠሟቸውን አደናጋሪ ጉዳዮች በተመለከተ ተጨማሪ ገለፃ ከመጠየቅ እንዳይታቀቡ ማበረታታት<br>• **የጥያቄ - መልስ ግንኙነት- ድህረ** ምንባብ ጥያቄዎች አራቱን አይነቶች ጨምሮ፡- በትክክል እዚያው (ምሳሹ በአንደኛው አረፍተ ነገር ውስጥ ይገኛል)<br>• **ማሰብ ማሰስ**፡- ( ምላሹ በቀረበው ፅሑፍ ውስጥ ይገኛል ነገር ግን ከአንድ በላይ የሆኑ አረፍተ ነገሮችን ማየት ይጠይቃል) | **ምልከታ** ተማሪዎች ክፍለ ጊዜው እየተካሄደ ወይም ክፍለ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ በቡድን ወይም በተናጠል ሲሰሩ አጫጭር ማስታወሻዎችን መፃፍ። መምህርቷ/ሩ በውስን የመማሩ ገፅታ ላይ ብቻ ፅብረቃ ማካሄድ<br>• **አቅርቦት** ተማሪዎች ግንዛቤያቸውን ለመምህር ወይም ለክፍሉ የሚያቀርቡበት እድል አላቸው።<br>➢ **ማጠቃለያና ፅብረቃዎች** ተማሪዎች ቆም እያሉ ፅብረቃ ማቅረብ፣ ስለሰሙት ወይም ስላነበቡት ነገር ትርጉም መስጠት፣ ከመማር ልምዳቸው በመነሳት የራሳቸውን ትርጉም መስጠት። እነዚህ ተማሪዎች ከይዘቱ ጋር በቀጥታ የተገናኘ ቋንቋ መጠቀም።<br><br>-ተማሪዎች አንድ ሰው ስላሳለፈው ነገር ሲናገር በማድመጥ አከናውኖ በነበሯቸው ተግባራት ላይ ምልከት ማድረግ። በመጨረሻም ይፈፅሟቸው ስለነበሩ ተግባራት አረፍተ ነገሮች መፃፍ። |

# ምዕራፍ ሰባት፡ የጥላቻ ንግግር
# (18 ክፍለ ጊዜያት)

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ተከታትለው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- ✓ አስተያየቶችን አዳምጠው መስማማትና አለመስማማታቸውን ይገልጻሉ፤
- ✓ ችግር ለመፍታት የሚያስችላቸውን ሁነት/ጥያቄ ያካተተ የጥላቻ ንግግርን የሚገልፅ ፅሑፍ ያነባሉ፤
- ✓ ቅፅሎችን ለይተው ይጠቀማሉ፤
- ✓ ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ✓ አንብበው ተመሳሳይ አስረጅ ጽሑፍ ይጽፋሉ፤
- ✓ “እና” እና “ግን”ን በመጠቀም ድርብ ዓረፍተነገሮችን ይጽፋሉ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• ፅሑፍ አዳምጠው መልዕክቱን ይናገራሉ።<br>• አንብበው ተመሳሳይ ፅሑፍ ያጎለብታሉ።<br>• የቃላትን አገባባዊ ፍቺ ይሰጣሉ።<br>• ቅፅሎችን ለይተው ይጠቀማሉ። | ማዳመጥና መናገር<br><br>ማንበብ<br><br>ቃላት<br><br>መፃፍ<br><br>ሰዋስው | **ስዕላዊ መግለጫዎች፡-**<br>ከንባብ በፊት፣ በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ስዕላዊ መገለጫዎቹ ድሮችን፣ የማወዳደርና የማነፃፀር ሰንጠረዦችንና መረጃን እይታዊ በሆነ መልኩ ለማዋቀር የሚረዱ ንድፋዊ መዋቅሮችን ሊያካትቱ ይችላሉ።<br>**ጣልቃ ገባዊ ምሪት**<br>ታሪክን ወይም አስረጅ ፅሑፍን (ልቦለዳዊ ያልሆነን) ለማንበብ ይረዳል።<br>**የገፀ ባህሪ መለያ**<br>በታሪኩ ሁነት ውስጥ ስለቀረበ ገፀባህሪ ለመረዳት ያግዛል። ሁነቶችን ለመረዳት ድጋፍ ያደርጋል (ማን፣ ምን፣ መቼ፣ የት፣ እንዴት)<br>**የዋና ሀሳብ ሰንጠረዥ**<br>ስለምንድን ነበር? ዝርዝሮቹስ ምን ነበሩ?<br>**የንድፍ ስዕል**<br>የታሪኩን ዋና ዋና ሁነቶች ለመዘገብ ያገለግላል | • ተማሪዎች አጠገባቸው ወዳሉ አንድ ወይም ሁለት ተማሪዎች በመዞር ምላሻቸውን ማጋራት<br>• ሂደቱን ለመከታተል መምህሩ በክፍሉ ውስጥ መዘዋወር<br>• **ፊትን ወደ ጓደኛ ማዞርና ማውራት**<br>ተማሪዎች ባጠገባቸው ወዳሉ አንድ ወይም ሁለት ተማሪዎች በመዞር ምላሻቸውንና እይታቸውን ማጋራት። (ሂደቱን ለመከታተል መምህሩ በክፍሉ ውስጥ ዞር ዞር ይላሉ።)<br>• **ስዕላዊ ውክልናዎች**<br>ተማሪዎች መረዳታቸውን ለማመላከት፣ለምሳሌ ስላነበቡት ታሪክ የፈጠሯቸውን ስእላዊ መገለጫዎች ማሳየት |

# ምዕራፍ ስምንት፡ ኤችአይቪ/ኤድስ (18 ክፍለ ጊዜያት)

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ትምህርት ተከታትለው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የተማሩትን ውስብስብ የቀለም መዋቅር የተላበሱ ቃላት ቀስ በቀስ እያደገ በሚሄድ አፈፃፀም ፊደላቱን ጠብቀው ይጽፋሉ፤
- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን አስረጅ ፅሑፍ ያነባሉ፤ ቀጥሎ የራሳቸውን ሀሳብ ይፅፋሉ፤
- የድርሰት አላባዊያንን ይለያሉ፤
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- ሳቢ እና ኢ-ሳቢ ግሶችን ይለያሉ፤
- ስነምዕላዳዊ ፍቺን ይለያሉ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• የምንባቡን ዋና ሀሳብ አዳምጠው ይለዩና በጉዳዩ ላይ ክርክር ያካሂዳሉ።<br>• አንብበው የራሳቸውን ሀሳብ ይፅፋሉ።<br>• የድርሰት መፃፍ አላባዊያንን ይለያሉ።<br>• ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ።<br>• ሳቢና ኢ-ሳቢ ግሶችን በመጠቀም አረፍተ ነገር ይመሰርታሉ።<br>• ስነምዕላዳዊ ፍቺን ይለያሉ። | • ማዳመጥና መናገር<br>• ማንበብ<br>• ቃላት<br>• መፃፍ<br>• ሰዋስው<br>• ሰዋስው | **ለይቶ ማውጣት (ማነፃፀር)**<br>ተማሪዎች የቃላት መዋቅርን ወይም የሆሄያት አሰዳደርን ማነፃፀር። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፡-<br>**የተለመዱትን ካልተለመዱት ጋር ማነፃፀር**<br>ትምህርቱ መጀመር ያለበት ቀደም ሲል የተማሩትን አሰዳደር የያዙ ተፃራሪ ቃላት በመጀመር አዲስ እየተማሩት ወዳለው አሰዳደር/መዋቅር መሄድ አለበት።<br>**የተዘረዘሩ ቃላትን መዋቅራቸውን ወይም አሰዳደራቸውን መሰረት በማድረግ መለየት**<br>የጋራ መዋቅርን ወይም ስደራን መሰረት በማድረግ ቃላትን ማቧደን የቀረበላቸውን መዋቅር ታሳቢ በማድረግ ምሳሌ የሚሆኑ ቃላትን መዘርዘር የቃላትን ስነ ምዕላዳዊ መዋቅር ተንትኖ የሚያቀርብ ዝርዝር ትምህርት | **ምሪታዊ ክለሳ**፡- የቀደመውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት መነሻ በማድረግ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ የተማሩትን ያጋራሉ፤ መምህሩ ይህንን መረጃ የዕለቱን ትምህርት አካሄድ ለመወሰን ይጠቀሙበታል<br>**አቅርቦት**<br>ተማሪዎቹ ለመምህሩ ወይም ለክፍሉ የግንዛቤያቸው እየጎለበተ መሄድን የሚያሳዩበት እድል ይኖራቸዋል<br>**የብጤ ክለሳ**<br>ተማዎች ፅሑፋዊ ተግባርን ካጠናቀቁ በኋላ፣ ከመምህሩ የሚሰጥ መመሪያን መሰረት በማድረግ ወረቀቶቻቸውን እርስበርስ በመለዋወጥ መተራረም። በመቀጠልም መምህሩ ወረቀቶቹን በመሰብሰብ አፈፃፀማቸውን መመልከት። |

# ምዕራፍ ዘጠኝ፡

# ልማዳዊ ተግባራት (18 ክፍለ ጊዜያት)

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተከታተሉ በኋላ፡-

- የሚነበብላቸውን ታሪክ ያዳምጣሉ፤
- በአስተያየቶች ላይ መስማማት አለመስማማታቸውን ይገልጻሉ፤
- ቀለል ያለና አጭር ታሪክን በማንበብ ዋናውን ሀሳብ ወደ ሰንጠረዥ ያሸጋግራሉ፤
- ካነበቡት ርዕሰ ጉዳይ ጋር የተያያዘ አጭር አንቀጽ ይጽፋሉ፤
- የሥራ ማመልከቻ ደብዳቤ ይጽፋሉ፤
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣሉ፤
- የሃላፊ ጊዜ ግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገር ይመሠርታሉ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• ምንባብን አዳምጠው ይገመግማሉ።<br>• አንብበው ፅሑፉ የያዘውን ሀሳብ በቃላቸው ይገልፃሉ።<br>• የማመልከቻ ደብዳቤ ይፅፋሉ።<br>• በአረፍተ ነገር ምስረታ የሃላፊ ጊዜን ይጠቀማሉ። | • ማዳመጥና መናገር<br>• ማንበብ<br>• ቃላት<br>• መፃፍ<br>• ሰዋስው<br>• ሰዋስው | **የቃል ፅሕፈት (ቃላትን)**<br>ሲነበብላቸው ተማሪዎች ቃላትን ማዳመጥ (ሊተኮር የተፈለገበትን መዋቅር ወይም የቃል ክፍሎች መሰረት በማድረግ)፣ ከዚያም ቃሉን ለመፃፍ መሞከር<br>**አረፍተ ነገሮች**<br>መምህር ተማሪዎቹ የሚፅፉትን አረፍተ ነገር ያነቡላቸዋል። አረፍተ ነገሩም አዲሱንና ቀደም ሲል የተማሩትን አሰዳደር እንዲከልሱ የሚያስችሉ ቃላትን የያዘ ነው። ተማሪዎቹም እነዚህን ቃላት በመለየት (የተለመደ ድምፅንና አቀማመጥን በማጤን) ማስመር<br>**ሞዴሎች**<br>አዋቂዎች መፃህፍትን ተማሪዎቹ ከሚማሩበት ደረጃ በላቀ ሁኔታ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በማንበብ ለተማሪዎች አርዓያ መሆን መቻል<br>**ድግግሞሻዊ የቃል ንባብ**<br>ተማሪዎች ተደጋጋሚ ንባብ እንዲያካሂዱ የሚያስችል እድል መፍጠር፤ ይህም ከመምህራን፣ ከጓደኞች እና ከወላጆች ድጋፍና ግብረ መልስን ያካተተ ሊሆን ይችላል | **አካላዊ ምላሽ**<br>ተማሪዎች ለጥያቄዎች አካላዊ እንቅስቃሴን በመጠቀም በተናጠል ምላሽ መስጠት።<br>አውራጣትን ማውጣት/ ማውረድ፣ ቡጢ መጨበጥ መዘርጋት፣ ጣትን እያወጡ ማሳየት የመሳሰሉት አንድን መልስን ሊያመለክቱ የሚችሉ ናቸው።<br>**ኢመደበኛ ክትትል**<br>መምህሩ ተማሪዎቹ ግጥም እንዲያነቡ ይሰጧቸውና በክፍል ውስጥ በመዘዋወር መደበኛ ባልሆነ መልኩ ክትትል ያደርጉባቸዋል |

# ምዕራፍ አስር፡
# ሴቶችን ማብቃት (18 ክፍለ ጊዜያት)

የሚጠበቁ ውጤቶች፡ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተከታተሉ በኋላ፡-

- አዳምጠው ፍላጎቶቻቸውን ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ይገልጻሉ፤
- ግለታሪክ ይጽፋሉ፤
- ተገቢ የአነባበብ ስልትን በመከተል ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ምንባብ ያነባሉ፤
- ቃላትን በምዕላድ ከፋፍለው ያሳያሉ፤
- በዓረፍተነገሮች ውስጥ ቀጥተኛ (ርቱዕ)ና ቀጥተኛ ያልሆኑ (ኢ-ርቱዕ) ተሳቢዎችን ይጠቀማሉ።

| ብቃቶች | ይዘቶች | የመማር ብልሃቶች እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች | ምዝና |
|---|---|---|---|
| ተማሪዎች፡-<br>• ንግግርን አዳምጠው ዕብረቃ ያካሂዳሉ።<br>• አንብበው ግለታሪክን ይፅፋሉ።<br>• ቃላትን በምዕላድ ደረጃ ይነጥላሉ።<br>• ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ተሳቢዎችን በዓረፍተነገር ምስረታ ይጠቀማሉ። | ማዳመጥና መናገር<br>• ማንበብ<br>• ቃላት<br>• መፃፍ<br>• ሰዋስው<br>• ሰዋስው | አነስተኛ ቁጥር ያለው የተማሪዎች ቡድን በተናጠል ወይም ደረጃ በደረጃ የቀረበውን ቃለ ተውኔት አዳምጦ ልምምድ ያደርጋል፤ በመጨረሻም ለተመላካች እየተተወነ ይቀርባል፤ በመሆኑም ገላጭና የተቀላጠፈ ንባብ እንዲኖር ይበረታታል።<br><br>**በጊዜ ማዕቀፍ የተቃኙ ተደጋጋሚ ንባቦች**<br>ተማሪዎች አጠር ያለ ምንባብን ለእያንዳንዱ ንባብ ጊዜ ይዘውለት በርከት ላለ ጊዜ ማንበብ፤ በማንበብ ፍጥነቱ የመጣውንም ለውጥ መመዘን። የንባብ ጊዜውም በሰንጠረዥ መገለፅ አለበት።<br><br>**ተደጋጋሚ እድሎች ለመፃፍ መስጠት።**<br>ቅድመ መፃፍ ተግባራት ከመፃፍ በፊት የሚከናወኑ እንደ መንደፍ፣ የታሪክ ካርታ ዝግጅት፣ ወይም ድር መሥራት ሀሳብ በማመንጨትና በማደራጀቱ ትልቅ ድጋፍ አላቸው። | ➢ **አቅርቦት**<br><br>**የርስበርስ ግምገም**<br>ተማሪዎች ፅሑፋዊ ተግባራትን ካጠናቀቁ በኋላ፣ የመመሀርን መመሪያ መሰረት በማድረግ የፃፉትን እየተለዋወጡ የእርስ በርስ እርማት ማካሄድ። በመጨረሻም መምህር ወረቀቶቹን መሰብሰብ<br><br>**የቡድን አፍልቆት**<br>መምህር አነስተኛ የተማሪ ቁጥር ባላቸው ቡድኖች የሚሰራ ስራ ይሰጣቸዋል፤ ሁሉም ተማሪዎች እየተሳተፉ ለመሆናቸው እርግጠኛ ለመሆንም ክፍል ውስጥ እየተዘዋወረ ይመለከታቸዋል። |

# ዋቢዎች

ማረው አለሙ። 2005። በሳል ድርሰት ማስተማሪያ። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ባየ ይማም። 2000። የአማርኛ ሰዋስው የተሻሻለ ሁለተኛ እትም። አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማ.ኃ.የተ.የ ግ.ማኅበር።

ደረጀ ገብረ። 1996። ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ጌታሁን አማረ። 1989። የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ዘሪሁን። 1992። የሥነጽሑፍ መሠረታውያን። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ፈንታሁን እንግዳ። 1992። የተውኔት ድርሰት አጻጻፍ ዘዴ። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።